
# ናይል



Nile 7th year; publication No.5; April,2021 ናይል 7ኛ ዓመት፣ ቁጥር 5፣ ሚያዚያ 2013 ዓ.ም

## የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የጤና ስፖርት ቡድን የቮሊቦል ውድድር አሸናፊ ሆነ

በወንዳለ ድረስ




የባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ የቮሊቦል ስፖርት ጤና ቡድን የዋንጫ ሽልማት በማግኘታቸው በዊዝደም ህንፃ ተገኝተው ደስታቸውን ሲገልፁ

በባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ባህል ቱሪዝም ስፖርት መምሪያ አዘጋጅነት ከየካቲት 20 እስከ ሚያዚያ 16/2013 ዓ.ም ድረስ በ14 መስሪያ ቤቶች መካከል በተካሄደው የጤና ስፖርት የቮሊቦል ውድድር ከፍተኛ ፉክክር የታየበት ሲሆን የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የቮሊቦል ስፖርት ጤና ቡድን አድማ ብተና የጤና ቡድንን 3 ለ 2 በማሸነፍ የዋንጫ ተሸላሚ ሆኗል፡፡ ቴሌ እና የባሕር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ለደረጃ ተጫውተው በቴሌ አሸናፊነት ተጠናቋል፡፡

ዶ/ ር ሰመኑ ተሾመ ከባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ የቮሊቦል ስፖርት ጤና ቡድን በኮከብ አሰልጣኝነት እንዲሁም አቶ አዱኛ አማረ በኮከብ ተጫዋችነት ተመርጠዋል፡፡

በውድድሩ አንደኛ ለወጡት የዋንጫ እና የወርቅ ሜዳሊያ የሰጡት በባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ ስፖርት አካዳሚ ዲን ዶ/ር ዳኛቸው ንግሩ ሲሆኑ በዕለቱ ለደረጃ ለተጫወቱ ተቋማት የባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ቮሊቦል አሰልጣኝ አቶ ምኒችል የኔአለም የሜዳሊያ እና የምስክር ወረቀት አበርክተዋል፡፡

ወደ ገፅ 3 ዞሯል




### በውስጥ ገፆች

4 ስፖርት ለህግ ታራሚዎች
11 ከዚያኛው ጫፍ
7 ከፍተኛ ትምህርት
8 Bahir Dar University in the eyes of...
9 ችግር ያዘጋው በር ...
15 የናይል እንግዳ ...




# ናይል

በኢንፎርሜሽን እና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዘዳንት ጽ/ቤት
በውስጥ ግንኙነት እና ኮሚኒኬሽን ክፍል የሚዘጋጅ ወርሀዊ ጋዜጣ

**ዋና አዘጋጅ**

ትዕግስት መኮንን

**ግራፊክስ ዲዛይነር**

ትዕግስት መኮንን

**ዘጋቢዎች**

ሙሉጎጃም አንዱዓለም
ወንዳለ ድረስ
ሙሉጌታ ዘለቀ

ትዕግስት ዳዊት

**ፎቶግራፈሮች**

ታምራት አታላይ
በሪሁን ታረቀኝ
ቤተልሄም ወርቅነህ

**አምደኞች**

አስቴር ሙሉ(ዶ/ር)
ምግበሩ ታደሰ
አስራት ደርብ
ሰው መሆን አላዛር

**አርታኢ**

አቶ ሀሰን ኡስማን

**መልእክተኛ**

መልሽው አጥናፉ
የመረጃ ዴስክ ባለሙያዎች

**ፀሀፊ**

መልሰው አደመ
አበባ ካሰው

**ሾፌር**

ላመስግን ጫኔ

**አባይ ማተሚያ ቤት ታተመ**
**መጋቢት 2013 ዓ.ም**

Contact us:-

https://www.bdu.edu.et
http://www.twitter.com/bdueduet
https://www.facebook.com/bduethiopia
http://www.linkedin.com/school/bahir-dar-university
+251583209653

# ርዕሰ-አንቀጽ

## ምርጫ እና የአገራችን ዕጣ ፈንታ

ምርጫ ዋናው የዜጎች ልዋላዊነት(popular sovereignity) መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዚህ መሰረት ዜጎች አስተዳዳሪዎቻቸውን በአብላጫ ድምፅ ለተወሰኑ ዓመታት የመሾም እና የመሻር መብት አላቸው፡፡

ይሁን እንጂ ዜጎች መብታቸውን ለመጠቀም እውቀትና መረጃ መሰነቅ ብቻም ሳይሆን የምርጫ ሂደቱ በራሱ ዲሞክራሲያዊ መርሆችን ማሟላት ይጠበቅበታል፡፡ ማለትም ሁሉን ዜጋ አካታች መሆን(universal suffrage)፣ አማራጭ እና ተመራጭ መኖር(alternatives)፣የመራጩ ፍላጎት እና ጉጉት መኖር፣ በተመራጩ መካከል እኩል የመደመጥና የመከበር መብት መጠበቅ፣ መራጭና ተመራጩ መተዋወቅ ና መረጃ አቅርቦት ፣ የድምፅ አሰጣጡ ሚስጥር በጠበቀ መልኩ መካሄድ፣ የምርጫ ዉጤቱ መቀበል፣ገለልተኛ ዳኝነትና የምርጫ አስተዳደር መኖር፣ እንዲሁም የዜጎችና የተመራጮች ደህንነትና ነፃነት መጠበቅ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ ቀላል የማይባል የምርጫ ታሪክ አላት፡፡ በተለይም ደግሞ በንጉሱ ዘመን ምክር ቤት ከተቋቋመበት ዘመን(1924 ዓም) ጀምሮ ምርጫ ሲካሄድ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን በምርጫው የፓለቲካ ድርጅቶች ያልተመሰረቱ በመሆናቸው ውድድሩ በግለሰቦች መካከል ነበር ፡፡

በወታደራዊ መንግስትም ዘመን የተካሄደው ምርጫ በፍፁም አምባገነን የሶሻሊስት ሥርዓት መንግስት ማዕቀፍ ውስጥ የተካሄደ ምርጫ በመሆኑ ዉድድሩ በአንድ ሪዮታለም ተገዥ በሆኑ ግለሰቦች መካከል የተገደበ ነበር፡፡

ትህነግ-ኢህአዴግ በሃይል ወደ ሥልጣን መንበር ከመጣ በኋላም ቢሆን አምስት ያክል አገራዊ ምርጫ ተካሂደዋል፡፡ ነገር ግን አንዳቸውም የመንግስትን አስተዳደር መለወጥ አላስቻሉም ነበር፡፡ በሁሉም ምርጫዎች ባይሆንም የተለያዩ ፓለቲካ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ተሳታፊዎች ነበሩ ነገር ግን ከአጃቢነት የዘለለ አሻራ ጥለው አላለፉም ማለት ይቻላል፡፡ በመወቅቱ መንግስት ተፎካካሪዎች ደካማ መሆንን እንደምክኒያት ይጥቀስ እንጅ ገዥው ፓርቲም የራሱ ችግር እንደነበረበት እሙን ነው፡፡ ኢህአዲግ አስመሳይ ድርጅት እንጂ ዲሞክራሲያዊ አልነበረም፡፡ ስለሆነም ምርጫዎች የባከኑ ትዕይንቶች ሁነው አልፈዋል፡፡


በአለፉት ጊዜያት የተካሄዱት ምርጫዎች በአንፃራዊነት ሁከትና ብጥብጥ የታየባቸው አልነበሩም፤ የ97ቱ ምርጫ በልዩነት የሚጠቀስ ነው፡፡ የ1997 ዓ.ም ምርጫ ተክትሎ መንግስት በዜጎች ላይ የወሰደው እርምጃ የከፋ ቢሆንም የምርጫው ዳፋ የአገር ህልዉና ላይ የደቀነው ፈተና አልነበረም፡፡

በመጪው ሐምሌ የሚደረገው ምርጫ በድህረ ትህነግ ዘመንላይ የሚካሄድ በመሆኑ በራሱ አውድ መገምገም ይገባዋል፡፡ መንግስት ዲሞክራሲያዊ መርሆችን በዋጅ ሁኔታ ምርጫው እንዲመራ ቁርጠኛ ከሆነ ታሪካዊ ውጤት ማስመዝገቡ አይቀርም፡፡ እንደ አሁን ቀደሙ አንድ የፓለቲካ ድርጅት በምርጫው 100% ላያሸንፍ ይችለል፡፡ በመሆኑም የጥምረት መንግስት ሊመሰረት የሚችልበት ዕድል ይኖራል፡፡

የሃገራችን አሁናዊ ሁኔታ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል፡፡ ዜጎች በማንነታቸው ምክንያት ጭፍጨፋና መፈናቀል እየገጠማቸው ነው፡፡ በፀጥታው ሰበብ ተፎካካሪዎች በፈለጉት ክልል ተዘዋውረው መምረጥ የማይችሉበት ሁኔታ የመኖሩን ያህል መራጮችም በቂ አማራጭ ሊቀርብላቸው አልቻለም፡፡

ከዚህም በላይ ትህነግ ለከፋፍለህ ግዛ ይጠቀምባቸው የነበሩ ተቋማት ፣ አሰራር እና አደረጃጀት ያልተቀየሩ በመሆኑ ድህረ ምርጫ ሁከት ማጋጠሙ አይቀርም፡፡ ሀገራችን ባለችበት ነባራዊ ሁኔታ ማንኛውም ሁከት በሃገር ልዋላዊነት እና ዜጎች ህልውና ላይ የማይሽር ጠባሳ ጥሎ የሚሄድበት መጥፎ ዕጣ ፈንታ ሊያጋጥም ይችላል፡፡

ስለሆነም ለዲሞክራሲ ተብሎ የሚደረግ የመሪዎች ምርጫ ጭራሽኑ ሃገር እንዳያሳጣን እጅ ለእጅ በመያያዝ ሃገራችንን እንታደግ



« …… ሀገሬ ኢትዮጵያ በዓለም ሸንጐ ላይ ፍርድ ተነፍጓት ስታዝን የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም፡፡ ….. ኢትዮጵያ ያለፉት ታሪኮቿ በትክክል እንዳስረዱት፣ ለነፃነቷና ለመብቷ፣ በኮሎኒያሊስት ጣሊያን ጋር በየጊዜው ስትዋጋ፣ ያሸነፈችው ብቻዋን ነው፡፡ የተጠቃችውም ብቻዋን ስለሆነ፣ አገሬ መቸውንም ለሚደርስባት አደጋ ከማንም እርዳታ አገኛለሁ ብላ አትጠብቅም፡፡ ዛሬም ሆነ ነገ ነፃነቷን ለመጠበቅ፣ ታሪኳን ለማስከበር አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ያለባት፣ እሷ ራሷ ብቻ ነች፡፡ ….. »

(ፎቶ U.N)

አክሊሉ ሀብተወልድ
(ኅዳር 21 ቀን 1949 ዓ.ም)

## የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የጤና ስፖርት ቡድን... ከገፅ 1 የቀጠለ

በባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ የስፖርት መምህር እና በዩኒቨርስቲው የቮሊቦል ስፖርት ጤና ቡድን አሰልጣኝ ዶ/ር ዘመኑ ተሾመ ዩኒቨርሲቲያችን ከሌሎቹ ተቋማት በተሻለ የስፖርት ማዘውተሪያ ያለው በመሆኑ አብዛኛው የስፖርት ቤተሰብ መደበኛ ልምምዱን ሳያቋራርጥ ጠንካራ የስፖርት እንቅስቃሴ በመስራቱ ማሸነፍ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

አክለውም በእለቱ ቀደም ብለው ከተካሄዱ የጤና ስፖርት ውድድሮች አንፃር ጠንካራ ፉክክር የተስተዋለበት ወድድር እንዳስተዋሉ ገልፀዋል፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የቮሊቦል ስፖርት ጤና ቡድን አምና እየመራ በኮቪድ ምክንያት ከመቋረጡ ባሻገር በ2011 ዓ.ም ሻምፒዮን መሆኑን አስታውሰው የአሁኑ ጨዋታ ጠንካራ ፉክክር እና የማሸነፍ ጉጉት የታየበት እንዲሁም የተጫዋቾች ጥንካሬ እና የስፖርት አካዳሚ ከፍተኛ እገዛ ታክሎበት፤ ውድድሩን የዩኒቨርሲቲው የቮሊቦል ስፖርት ጤና ቡድን ማሸነፍ መቻሉን ዶ/ር ዘመኑ ገልፀዋል፡፡

# ሠሞነኛ

ይህ አምድ ከዜናዎች በተጨማሪ ወቅታዊ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ ሀተታዊ ፅሁፎች ይቀርብበታል

## ስ ፖ ር ት ለ ህ ግ ታራሚዎች



ታራሚዎች የመረብ ኳስ በመጫዎት ላይ

በሙሉጎጃም አንዱአለም

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ ከባህር ዳር ከተማ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደርና ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በመተባበር ታራሚዎች የተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲያከናውኑ ለሁለት ወራት የሚቆይ የስፖርት እንቅስቃሴ ለማካሄድ በማረሚያ ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ የመክፈቻ ስነ-ስርዓቱ ተከናወነ::

ለመርሃ ግብሩ ታዳሚዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን ያስተላለፉት የማረሚያ ቤቱ መምሪያ ኃላፊ ኮማንደር ውብሸት መኮነን በማረሚያ ቤቱ የሚገኙት ታራሚዎች ከ75% በላይ የሚሆኑት ወጣቶች በመሆናቸውና ስፖርት ለአካላዊም ሆነ ለአእምሮአዊ ብልፅግና ጉልህ ፋይዳ ስላለው ሁሉም ታራሚ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ በማድረግ የቅጣት ጊዜውን ጨርሶ ወደ ማህበረሰቡ ሲቀላቀል ብቁ ዜጋ እንዲሆን ዩኒቨርሲቲው በማሰብ መርሐ ግብሩን ስላዘጋጀው የላቀ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የስፖርት አካዳሚ ዲን ዶ/ር ዳኛቸው ንግሩ በበኩላቸው ጥሪውን አክብረው ለመጡ ታዳሚዎች የእንኳን ደህና መጣችሁና የምስጋና መልዕክታቸውን አስተላልፈው ስፖርታዊ ውድድሩ ለሁለት ተከታታይ ወራት የሚቆይ መሆኑና ታራሚዎች የቅጣት ጊዜአቸውን ጨርሰው ሲወጡ በአካልም ሆነ በአእምሮ በቅተው እንዲገኙ እንዲሁም ከውድድሩ መልስ ብቁ ዜጋ ይሆኑ ዘንድ ታልሞ የተዘጋጀ ፕሮግራም መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

ጨዋታው በይፋ መጀመሩን ያበሰሩት የዩኒቨርሲቲው ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ ፕሬዘዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈረው ስፖርት ጤናን፣ፍቅርን ፣ሰላምን፣አንድነትን ስለሚያጎለብት ታራሚዎች የቅታት ጊዜአቸውን ጨርሰው እስከሚወጡ መነቃቃትን ለመፍጠር አካዳሚው ላበረከተው አስተዋፅኦ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

ዶ/ር ተስፋዬ አክለውም ዩኒቨርሲቲው ለወደፊት ከስፖርቱ በተጨማሪ ታራሚዎች በሌሎች ሙያዎች እራሳቸውን አብቅተው እንዲወጡ የሚያደርጉ ተግባራትን እንደሚያከናውን ቃል ገብተው የስፖርት ውድድሩ የማንቂያ ደወል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በመክፈቻው ከተደረጉ ጨዋታዎች መካከል ዞን 1 ከዞን 3 ጋር ባደረገው የገመድ ጉተታ ጨዋታ ዞን 1 ሁለት ለባዶ አሸንፏል፤በተጨማሪም ዞን 4 ታራሚዎችና የፖሊስ አባላት ባደረጉት የመረብ ኳስ ጨዋታ ታራሚዎች የፖሊስ አባላትን ሁለት ለባዶ አሸንፈዋል፡፡

ከአዲስ አምባና ከቤንማስ ሆቴል ለህግ ታራሚዎች የተሰጠ የስፖርት ትጥቅም ርክክብ ተፈፅሟል፡፡

## የባድሜንተን ስፖርት ውድድር በባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ

በትዕግስት ዳዊት

የ2013 ዓ.ም የባድሜንተን ስፖርት የኢትዮጵያ ሻምፒዮና ውድድር ከሚያዚያ 2/2013 ዓ.ም እስከ ሚያዚያ 10/2013 በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ዘንዘልማ ግቢ ሲካሄድ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ በውድድሩ 5 ክልሎች እና 2 ከተማ አስተዳደሮች ማለትም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ ከኦሮምያ ክልል፣ ከአማራ ክልል፣ ከሲዳማ ክልል፣ ሶማሌ እና ሃረሪ ክልል የመጡ ስፖርተኞች ተሳትፈውበታል፡፡ ውድድሩ በኦሮሚያ ክልል አሸናፊነት ተጠናቋል፡፡



አቶ በሀር ጅብሪል የኢትዮጵያ ባድሜንተን ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት በውድድሩ መዝጊያ ተገኝተው ውድድሩ ቀጣይ እና ተመጋጋቢ እንዲሆን በቀጣይ ጊዜያትም በትኩረት መስራት እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡ ፕሬዚዳንቱ አክለውም ስፖርታዊ ጨዋነት ችግሮችን ለማማሻሻል ስፖርተኞች የውድድሩን ህግ ጠብቀው በመወዳደር ብቁ ሆነው እና ሃቀኝነትን ይዘው እንዲጓዙ ቀዳሚ መሆን እንዳለባቸው አሳስበው በውድድሩ ውጤት ሳስመዘገቡ እና ተሳትፊ ለነበሩ ሁሉ የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ውድድሩ ከተለያዩ ክልሎች የመጡ ወጣቶችን አንድ ላይ የሚያገናኝ በመሆኑ ብሄር ብሄረሰቦች በጠባብ አዳራሽ ተገናኝተው ወጋቸውን ባህላቸውን እንዲሁም ታሪካቸውን የሚለዋወጡበት በመሆኑ ትልቅ ትርጉም እንደነበረው ተገልጿል፡፡

ውድድሩን የክልሉ ባድሜንተን ፌዴሬሽን እና የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስፖርት አካዳሚ ያስተባበሩት ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ግብርና እና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅን ደግሞ ለልኡካን የመኝታ እና ጠቅላላ አገልግሎት በመስጠት ከፍተኛ ድጋፍ በማድረግ ወድድሩ የተሳካ እንዲሆን ሚናቸው ላቅ ያለ ነበር፡፡

# አቶ አሊ ከገፅ 14 የቀጠለ

ከገፅ 14 የቀጠለ

በወቅቱ ከዘንዶ እና ከአንበሳ ጋር ከገበሬው ጋር ፍቅር መስርተን ያሳለፍንበት ወቅት ነው፡፡

ለምሳሌ እኔ ከዘማቾች ውስጥ ሁለት ጓደኞቼን ገብሬያለሁ አንዱን ዘንዶ ሲበላው አንዱን ደግሞ በጎርፍ ተወስዶ ሞቷል፡፡ ለሀገር የተከፈለው አኩሪ መስዋዕትነት ነው፡፡ ሁለተኛው አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጋይዳንስ ካወንስሊንግ ሁኜ ሰርቻለሁ፡፡ የሰውን አእምሮ በዱላ መግዛት አይቻልም ልጆችን በፍቅር ነው ማምጣት ያለብን ዛሬ የገረፍነው ተማሪ ነገ ከረፈደበት በዛው ይቀራል እያልን ነበር የምናስተምር፡፡

በጨረሻም የሁለተኛ ደረጃ ጋይዳንስና ካውንስለር የሆኑትን ሰበሰብኳቸውና ከዞን አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር ምን እናድርግ? የሰውን አዕምሮ ከዱላ ይልቅ በምክር መመለስ እንዴት ነው የሚቻለው? ከ200 ገፅ በላይ የጋይዳንስ ማንዋል አዘጋጅተን ማንዋሉን ለሁሉም ትምህርት ቤቶች አደልን:: በተ ማሪው ላይ ይደርስ የነበረው ቅጣት ቀስ በቀስ እየቀነሰ መጣ፡፡ ትምህርት ቤቶችም የጋይዳንስ ካውንስለሮች የቅንጅት ስራ ኮሚቴ አቋቋሙ በየቦታው ስልጠና መስጠት ጀመርን ርዕሰ መምህራንን ስልጠና መስጠት የጋይዳንስ ካውንስለር አደረጃጀት አቀረብን፡፡

ናይል፡- ትውስታዎች ካሉ ቢያጫውቱን?

አቶ አሊ: ኤርትራ ቆይቻለሁ ፣ቀይ ኮከብ ሲዘመትእኔ ኤርትራ ነበርኩ፡፡እዚያ ላይ ያጋጠመኝ በወቅቱ ሦስት መቶ የሚሆኑት የጀበሀ አባላት እጁ ሰጡ ተብሎ ኩናማ አካባቢ የክፍለ ሀገሩ ዋና አስተዳዳሪ የደንነት ሀላፊው የጦሩ መሪዎች ከፓርቲ ኮሚቴዎች እኔ ‘ዳሽ-6’ በምትባል ሄሊኮፕተር ተነሳን አስመራን እንዳለፍን የሄሊኮፕተሯ አንደኛው ሞተር ጠፋ ከዚያ እኔ በጣም ተደናገጥኩ ለካ የጦር መኮንኖች በአደጋ ጊዜ የሚወጥ ከኒና ይዘዋል አደጋው የማይቀር ከሆነ ክኒናዋን ወስዶ እራሱን ይገድላል፡፡ እኔ ሲቪል ስለሆንኩ ይህንን አላውቅም፣ ዝግጅቱም የለኝም ሁሉም ከኒናውን አዘጋጅቷል ፣በመጨረሻም ፓይለቱ እንደምንም በአንድ ሞተር መሬት ላይ በሰላም አሳረፈው ሳቅ…፣ በተረፈ ሌላው አሳዛኝ ገጠመኝ በቀይ ኮከብ ጊዜ ከርከብት ተሚባል አካባቢ ከፍተኛ ጦርነት ተደርጎ የሁለቱም ወገን አልቆ አካባቢው እሬሳ በሬሳ ሆኖ በአሳቃቂ ሁኔታ የቆሰሉት

ደግሞ እባክህ ወንድሜ ግደለኝ ጨርሰኝ አትለፈኝ የሚሉ ቁስለኞችን በህሊናዬ ምንጊዜም አልረሳውም፡፡

ናይል፡- የእረፍት ጊዜዎን በምን ያሳልፋሉ?

አቶ አሊ፡- እንግዲህ ጊዜዬን የማሳልፈው አንደኛ መጠጥ አልጠጣም ውጭ አላመሽም በጣም አስቸኳይ ስራ ከሌለኝ ሁሌም አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ቤቴ ነኝ ፤ በተረፈ የልጆቼ ፍቅር ስላለኝ ልጆቼን አስጠናለሁ አስተኛለሁ ቀሪ ጊዜዬን

**“ የትምህርት ፍኖተ ካርታ አፍርቶ መሬት ረግጦ የህዝብን ችግር የሚፈታ ሆኖ ምሁራን ተ ረ ባ ር በ ው በ ት በህይወት ዘመኔ ማየት እፈልጋለሁ::’**

ደግሞ አነባለሁ፤ በነገራችን ላይ መፅሐፍ ማንበብ በጣም እወዳለሁ:: ያ ስርዓት ማንበብና መፃፍ አስተምሮኛል -ሳቅ- ከዚህ የተነሳ መፅሀፍ ማንበብ በጣም እወዳለሁ፡፡

**ናይል፡** በመጨረሻም ቀረ የሚሉት መልዕክት ካለ እድሉን ልስጥዎ?

አቶ አሊ፡ እኔ እንደጠቀስኩት የትምህርት ጥራትን ለማምጣት ሁለት ነገሮች ላይ ትኩረት መደረግ ያለበት ይመስለኛል፡፡

አንደኛው ስርዓተ-ትምህርቱ ነው:: የትምህርት ፍኖተ ካርታ አፍርቶ መሬት ረግጦ የህዝብን ችግር የሚፈታ ሆኖ ምሁራን ተረባርበውበት በህይዎት ዘመኔ ማየት እፈልጋለሁ:: እኛው የተከልነው ችግኝ ነው መብቀል የሚችለው ከውጭ ያመጣነው ስርዓተ ትምህርት ለኛ አልሆነም አይተነዋል፡፡ ሁለተኛው ከምልመላው ጀምሮ መምህራን ስልጠና ላይ ትልቅ ትኩረት መሰጠት አለበት ድሮ በደርግ ጊዜ የድኅማ መምህር መቅጠር ከጀመረ ጊዜ ጀምሮ ነው የመምህርነት ጥራት የሞተው አሁንም ወደ መምህሩ መመለስ አለብን ይህ ከምን ይጀምራል ብትለኝ ከምልመላ ጀምሮ በትኩረት መሰራት አለበት ዩኒቨረሲቲ ሁሉም ሂዶ ውጤት የሌለው ተማሪ ባጣ ባጣ መምህርነት አላጣ እንዳይል በመምህራን ግንባታ ላይ በትኩረት መሰራት አለበት እላለሁ፡፡

**ናይል፡** አቶ አሊ ስለነበረን መልካም ቆይታ በናይል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ስም በጣም አመሰግናለሁ?

**አቶ አሊ፡** እኔም እጅግ በጣም አመሰግናለሁ፡፡



## ከዚያኛው ጫፍ ... ከገፅ 11 የቀጠለ

አ ክ ቲ ቭ
ነኝ እያልሽ ነው?›› ብዬ ፃፍሁ፡፡

‹‹ ምነው ይህንን ለማለት ይህንን ያህል ቆዩህ፣አላመንከኝም ማለት ነው ወይስ . . . ?››

‹‹ወይስ ምን?››

ሁሉንም ንገሩኝ አትበል እንጅ››

‹‹ለምንኛውም አሪፍነቴን ለማየት ከፈለግህ፣ሞክረኝ››፡፡

ንግግሯ ስሜቴን እያጋለው ቢሆንም፣ ቸኮላዋ ግን ጥሩ እንዳይሰማኝ አድርጎኛል፡፡ በእርግጥ እኔ ለእንደዚህ ያለ ነገር አዲስ ብሆንም ጓደኞቼ የዛሬ ሴቶች እኮ . . . ከፈጣጣነታቸው ችኮላቸው፣ ከፈለጉ ፈለጉ ነው፣መግደርደር ድሮ ቀረ ፤ እያሉ ሲያወሩ ብዙ ጊዜ ሰምቻለሁ፡፡ ይህቺም እንግዲህ የዘመኑ ሴት መሆኗ ነው፡፡

‹‹የት ልይሽ አልኳት››

‹‹የት ነው ያለኸው?፣አዲስ አበባ ነህ አይደል?››፡፡

‹‹በምን አወቅሽ? ሰይጣን አረባለሁ ልበልህ?››

‹‹እሺ ፣አንቺ የት ነሽ?››

‹‹አዲስ አበባ››

‹‹ነገ ስንት ሰዓት እንገናኝ?››

‹‹እንዴ! ተው እንጅ እንዲህ አትቸኩል›› ቸኩላ ካስቸኮለችኝ በኋላ፡፡


‹‹ቆይ አስቤ ልንገርህ›› ብላ ፀጥ አለች፡፡

ጠበቅኋት፣ጠበቅኋት አልፃፈችም፣ ሰውነቴ እንደሞቀ ነው፤ ወደ ራሴ ለመመለስ ሞከርሁ፤ ይህን ጊዜ ከምኝታ ቤታችን አጠገብ ከሚገኘው ሻወር ቤት ውሀ ሲፈስ ተሰማኝ፡፡ ባለቤቴ አልተኛችም ማለት ነው፡

አንድ ሀሳብ መጣልኝ፣ ከሻወር ቤት ከመመለስዋ በፊት ወደ መኝታ ቤቷ መሔድ፣ እንደገባች አቅፋታለሁ፣እስማታለሁ፣ ዛሬ የግድ ነው አልሁ፡፡ ‹‹ሚስቶች ያለፈቃዳቸው በባሎቻቸው ይደፈራሉ፡፡ ገለመሌ፣ ደርሶ ፈረንጅ መሆን፣ እኔ ሀበሻ ነኝ፡፡ በገዛ ሚስቴ ማንስ፣ ምን አገባው? ሃሳቤን ወደ ተግባር ለመቀየር በፍጥነት ከአልጋዬ ላይ ተስፈንጥሬ ተነሳሁና ሚስቴ ወደምትተኛበት ክፍል ገባሁ፡፡ ከአልጋው አጠገብ የተቀመጠው የንባብ ጠረንጴዛ በወረቀት ተሞልቷል፡፡ ኮምፒውተሯ ክፍት ነው፡፡ የፌስ ቡክ ፔጅ ተከፍቷል፡፡ አልጋው ላይ ተቀምጬ መጠበቅ ጀመርሁ፡፡ ዘላለም የጠበቅሁ መሰለኝ፡፡

እስክትመጣ ድረስ ብዬ ኮምፒውተር ለመነካካት አይኔን ወደ ኮምፒውተሩ ሳቀና ያየሁት ነገር ግን ሰውነቴን እንደበረዶ አቀዘቀዘው፡፡






## እጅ ከምን

በዚህ አምድ የዩኒቨርሲቲው ባልደረቦች እጅ ከምን ስንል አለን የምትሉት ለአንባቢ የሚበቃ ፅሁፍ ይስተናገድበታል

# ከፍተኛ ትምህርት (Higher Education) - መካነ አእምሮ (University)

በአስራት ደረብ

(PhD candidate in Higher Education Leadership and Management)

Email: asrat.dereb@bdu.edu.et, or asd.dereb5@gmail.com

ቅድመ ሃሳብ፡- በዚህ መጣጥፍ ውስጥ በተከታታይ ስለከፍተኛ ትምህርት ምንነት፥ እድገት፥ ተልዕኮ በአጠቃላይ የሴክተሩን አስተዳደድና አመራር ጥበብ በፅንሰ ሃሳብና በተግባር ምርምር የተደገፈ ፅሁፍ አቀርባለሁ:: ውድ አንባብያን በማቀርበው ሃሳብ ላይ አስተያየት፥ጥያቄ፥ ተቃርኖአዊ ሃሳብ ካላችሁ ከላይ ባስቀመጥኩት ኢሜል ሃሳባችሁን መላክ ትችላላችሁ:: ፅሁፎቼ ሃሳቤን በደንብ ይገልፅልኛል ብየ ባመንኩበትና ተድራሽነቱን በደንብ በለየሁበት አግባብ በአማርኛም በእንግሊዘኛም ቀያይጩም ሆነ በተናጥል እንደማቀርብ ከወዲሁ ለማሳወቅ እወዳለሁ::

መንደርደሪያ ሃሳብ፡ ከፍተኛ ትምህርት (Higher Education)

ከፍተኛ ትምህርት ምን ማለት ነው? እነማንንስ ያካትታል?

### ከፍተኛ ትምህርት (Higher Education)

ከፍተኛ ትምህርት ሲባል ከድህረ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት (Post-secondary education) በኃላ ያሉትን የትምህርትና ስልጠና ሥርዓት ያካተተ ነው:: ይህም ማለት የተለያዩ የኮሌጅ ትምህርቶችን፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናዎችን እንዲሁም የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ኘሮግራሞችን ያካተተ ነው:: አተረጓጎሙ በእርግጥ ከሃገር ሃገር ልዩነት ሊኖረው ቢችልም አብዛኛዎቹ ሃገራት ከላይ የተጠቀሰውን አረዳድ ይከተላሉ:: የዚህ ጽሁፍ አላማ ሁሉንም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሁኔታ ማውራት ሳይሆን የጽሁፉ ይዘት በአብዛኛው የሚያተኩረው ዩኒቨርስቲዎች (መካነ አእምሮ) ላይ ይሆናል:: ይሁን እንጂ ሁሉንም የትምህርት እርከን የጋራ የሚያደርጉ ጉዳዮች ሲገኙ ግን ሃሳብ ከመስጠት ወደ ኂላ አልልም:: ለዚህ ፅሁፍ ግን ከፍተኛ ትምህርት ስንል ዩኒቨርሲቲን ወይም መካነ አእምሮ ተብሎ የሚጠራውን የትምህርትና ስልጠና ስርዓት እንዲሁም የተቋማትን አደረጃጀት ማለታችን ነው::

### ትምህርት ቤት (School)

ትምህርት ቤት የሚለውን ትልቅ ሃሳብ እዚህ ላይ ማንሳት የተፈለገበት ምክንያት የዩኒቨርስቲን ዝርዝር ጉዳይ ከማንሳቴ በፊት ለሁሉም የትምህርት እርከኖች የሚያገለግል ብርቱ ሃሳብ ለማንጸባረቅ ፈልጌ ነው:: ቅድመ መደበኛም ትምህርት ቤትም እንበለው የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም እንበለው ዩኒቨርሲቲ ሁሉንም ት/ቤት (School) እንላቸዋለን:: ነገር ግን ሁሉንም ትምህርት ቤት እንበላቸው እንጅ እያንዳንዱ የትምህርት እርከን በይዘትም ይሁን በአደረጃጀት እንዲሁም በተልዕኮ የየራሳቸው የሆነ መለያ ባህርይ አላቸው::

ትምህርት ቤት የሰው ልጅ በተፈጥሯዊ ሁኔታ ከአባት ከእናቱ ከተገኘ በኃላ በማህበራዊ ዕሴት ቅንብብ ውስጥ በሚኖረው መስተጋብር በዕውቀት በልጽጎ፣ በክህሎት ልቆ በአመለካከት ተለውጦና ገዝፎ የአመክዮ ችሎታው ዳብሮ የሚወጣበት ትልቅ ተቋም ነው:: ለዘህም ነው ባለሙያዎች “A School is an industry in which human being is cultivated and made” የሚሉት:: በመሆኑም የሰው ልጅ ከልጅነቱ እስከ ጉልማሳ ህይወት መጀመሪያ ያሉትን ዘመኖቹን በትምህርት ቤት ውስጥ ያሳልፋል:: ትምህርት ቤት ከመኖሪያ ቤታችን / መጠለያችን/ ቀጥሎ የሚገኝ ቤታችን ነው ልንለው እንችላለን (School as a home away from home) ::

መሪ ቃል (motto) ከላይ ያነሳሁትን ሃሳብ በሚከተለው መሪ ቃል (motto) ላጠናክረው:: “A school should be an example of good home” የዚህን አባባል ውርስ ትርጉም ስናየው “ትምህርት ቤት የጥሩ መኖሪያ ቤት ምሳሌ መሆን አለበት” እንደማለት ነው:: እዚህ ላይ ትምህርት ቤትን በጥሩመኖሪያ ቤት ምስለት (Analogy) ተገልጾ እናገኘዋለን:: እንግዲህ እዚህ ላይ አንድ ብርቱ ጥያቄ ልናነሳ እንችላለን:: የጥሩ መኖሪያ ቤት ወይም “good home” መገለጫዎቹ ምንድን ናቸው የሚል ጥያቄ እናነሳለን:: ስለዚህ የጥሩ ቤት መገለጫወችን በማየት ከዛ ሃሳቡን ወደ ትምህርት ቤት እናመጣና በዛ መነጽር ደግሞ የዩኒቨርሲቲያችን ነባራዊ ሁኔታ እናያለን

ማሳሰቢያ፡- በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ የምናነሳቸውን ነገሮች ሁሉ ወደራሳችን ተቋም ነባራዊ ሁኔታ በማምጣት ነገሮችን፣ ማየት፣ መገምገምና በአገኘነው ግብረ መልስ ተመስርተን አሠራርን ማሻሻል፣ ማስተካከል፣ ማበልፀግ የዚህ ፅሁፍ ዋና አላማ ስለሆኑ በዚህ ቅኝት እንድናየው አፅንኦት ለመስጠት እፈልጋለሁ::

ወደ ዋናው ቁምነገር ስንመለስ ጥሩ መኖሪያ ቤት (Good Home) በሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ሊዳሰስ ይችላል:: ነሱም 1ኛ ቁሳዊ ስሬት (physical makeup) ሲሆን 2ኛው ደግሞ ስነ ልቡናዊ ስሬት (Psychological makeup) ነው::

ቁሳዊ ስሬት (physical makeup)፡ ይህ ማለት ጥሩ መኖሪያ ቤት የቁሳዊ አካባቢው (physical environments) እጅግ ያማረ፣ ቤቱን ከውስጥም ከውጭም በምንመለከትበት ጊዜ ጽዱና ውብ የሆነ ቤት ነው:: በተጨማሪም የቤቱ እቃዎች አደራደር ማራኪ፣ አካባቢውንፁህ ፣ ቤቱ ነፋሻ አየር ያለው፣ ቤቱም እንደ ዓቅሙ መሟላት ያለበትን የቤት እቃዎች የያዘ ባጠቃላይ ደስ የሚል ቤተሰቡን ሰብሰብ አድርጎ መያዝ የሚችልና የቤተሰቡ አባላት ቤታችውን ትተው እንዲወጡ ምክንያት የማይሰጥና ከቤት አትውጡ አትውጡ የሚል አደረጃጀት ያለው ቤት ማለት ነው::

ስነ-ልቡናዊ ስሬት (Psychological makeup) ፡ በስነ-ልቡናዊ ረገድ ሲታይ ደግሞ ጥሩ መኖሪያ ቤት ሰላም የሰፈነበት፣ በቤተሰቡ አባላት መካከል መከባበር፣ መተጋገዝና መደማመጥ ያለበት፣ ፍቅር የተሞላበትና ደስተኛ ቤተሰብ ያለበት ቤት ማለት ነው:: የቤተሰቡ አባላት በእድሜ፣ በልምድና በትምህርት ደረጃቸው የየራሳቸውን ሃላፊነት የሚወጡ፣ ችግርንም ደስታንም እንደአመጣጡ መወጣት የሚችሉ ባጣቃላይ ጠንካራ ማህበራዊ መስተጋብር ያለበት ቤት ማለት ነው::

ከላይ ያነሳናቸውን ሁለቱን ዐውዶች ወደ ትምህርት ቤት ስናመጣቸው ጥሩ ትምህርት ቤት ቁሳዊ አካባቢው (physical environments) እጅግ ንፁህ የሆነ፣ የመማሪያ ክፍሎች ንጽህና የክፍሎች አደረጃጀት፣ የወንበሮች አይነትና አቀማመጥ፣ የጥቁር ሰሌዳ (white board) ዝግጁነት፣ መስኮቶች አየር የማሰገባትና የማስወጣት ጥራታቸው፣ የግቢው ውበት፣ አረንጋዴነት ደረጃየምናይበት መነጽር ነው:: የመምህራንና ሰራተኞች የቢሮን ደረጃ፣ ወንበር፣ ጠረንጴዛን እንዲሁም የቤተሙከራዎችና የቤተ መጻህፍትን ንጽህና አደረጃጀት ያካተተ በአጣቃላይ ምድረ ግቢው ተማሪዎችንም ሆነ መምህራንና ሰራተኞችን ለረጅም ሰዓት ያለመሰልቸት ይዞ የማቆየት አቅም ያለው አካባቢ ማለት ነው::

በስነ-ልቡናዊ ረገድ ደግሞ ጥሩ ትምህርት ቤት በት/ቤት አመራሩና በመምህራን ፣ በመምህራንና በመምህራን፣ በመምህራን እና በተማሪዎች፣ በተማሪዎች እና በተማሪዎች መካከል በአጠቃላይ በት/ቤቱ እና በተለያዩ አጋር አካላት መካከል የመተባበር፣ የመተሳሰብ፣ የመደጋገፍ፣ በጋራ የመስራት፣ አብሮ የማደግን መንፈስ የያዘ ተቋም ማለት ነው:: ባጠቃላይ በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ መካከል ትርጉም ያለው መስተጋብር (meaningful interaction) ያለውና ባለ ራዕይ ትምህርት ቤት ማለት ነው::

መ ካ ነ አ እ ም ሮ ( ዩ ኒ ቨ ር ስ ቲ ዎ ቻ ች ን ) ፡

ዩኒቨርሲቲዎቻችን እንደ ትምህርት ተቋምነታቸው ከላይ ባነሳናችው በሁለቱ መሠረታዊ ነጥቦች ሲፈተሹ እንዴት ይታያሉ? Can they be an example of good home? መልሱን ለእያንዳንዱ አንባቢ ልተወው::

ዩኒቨርሲቲ ወይም ደግሞ መካነ አእምሮ ተብሎ የሚጠራው የትምህርት ተቋም ከስሙ እንደምንረዳው የሰው ልጅ አእምሮ በትምህርትና ስልጠና የሚሰላበት፣

ወደ ገፅ 12 ዞሯል

ናይል 7ኛ ዓመት፣ ቁጥር 5፣ ሚያዚያ 2013 ዓ.ም

# ባህረ_ሃሳብ

ይህ አምድ የተለያዩ የሀሳብ ልዩነቶችን የሚያንፀባርቁ ፅሁፎች፣ ትዝብቶች እና ክርክሮች ይቀርብበታል

# BAHIR DAR UNIVERSITY IN THE EYES OF AN EXPATRIATE PROFESSOR

*By Migbaru Taddese*
*MA student , Media and Communication department*

**Nile:** I am delighted to have met you, and on behalf of Nile and myself, I thank you for your time.

**Dr. Neela:** Thank you! It is my pleasure.

**Nile:** Would you introduce yourself?

**Dr.Neela:** I am Dr. Neela Satheesh, Associate Professor from Faculty of Chemical and Food Engineering, Bahir Dar University Institute of Technology.

**Nile:** I am trying to explore your views and opinions about Bahir Dar University and particularly BiT (Bahir Dar institute of Technology), the campus where you are working. Let us begin with your gut feeling about Bahir Dar University?

How did you end being here? When and how did you decide to join the staff here?

**Nile:** Actually, I wanted to come here not directly from India. I was working at Jimma University. I joined Jimma University like any other foreigner. By that time, I did not have a clear and adequate information about the country, the people and so forth.

What I did as a foreigner is try to find people who have been to Ethiopia, so I took their opinion. Then, I got a mixed feeling. Some people advised me not to go while others advised me otherwise. Then, I went into exploring deep about Ethiopia. I explored in detail about the social, economic and political conditions of Ethiopia from different data sources. I, then, decided to move to Ethiopia with confidence and joined Jimma University. Now, I feel that the country is excellent; it is a very beautiful country.

The people i,n Jimma and Jimma University are welcoming, friendly and cooperative. So, I happily stayed in Jimma for four years. Meanwhile, I visited Bahir Dar as a tourist in March 2015. In my visit, I met my colleagues and even went to Wisdom Tower. I stayed at Poly Campus for a short while and visited the different departments in it. I was very attracted by Bahir Dar City. This is because Bahir Dar City looks like Indian cities in terms of arrangement and organization. So, after two years in Jimma University, I went back to India where I met recruiters. I liked them. Then, I came here. I joined Bahir Dar University in September 2017. It was very good for me that I had been to Bahir Dar before I joined the University. Thus, I came here and am working with full confidence. I do not have much problem here because I know the location, the people, the University, the city. I am very happy to have come and joined Bahir Dar University. This is why I quit Jimma University and decided to join Bahir Dar University. So, I am proud to be a staff here.

> **“The University should meet our needs. I think the main thing is that expatriates are facing critical problems with respect to housing. This is because staying in private homes for expatriates is very difficult. We often are exploited. I suggest that the first thing the University should do is solving this issue**

**Nile:** Coming to Bahir Dar city, being in the down town, have you come across a kind of unforgettable emotional experience you would like to share with us like intercultural challenges in the office politics or anything?

**Dr. Neela:** Absolutely. My home is in kebele 13, far from the university. I used to go home from Poly because I had my family waiting for me there. I often travelled by taxi every three or four times a day. In most cases, I find the people of the city cooperative and friendly. If I have a kind of confusion, ask for help and get the support I want. The people are supportive. However, in one of the days, I ran into a crazy guy in the evening as I took my family out for dinner.

While we were walking right in the middle the guy came straight and initiated a bust up. Luckily there was an Ethiopian, whom I did not see, watching and closely monitoring what was going on, and he jumped into the middle and saved me and my family.

**Nile:** What do think should the university do with respect to expatriates like you?

**Dr. Neela:** The University should meet our needs. I think the main thing is that expatriates are facing critical problems with respect to housing. This is because staying in private homes for expatriates is very difficult. We often are exploited. I suggest that the first thing the University should do is solving this issue.

**Nile:** you mean there are land lords in the city who abuse you?

**Dr. Neela:** Exactly! The landlords try to exploit us. Sometimes security is the issue and sometimes rent is another issue. They may not follow the agreement. Second thing is that the fact that the office it is too far from home is a very big problem. We spend most of our productive hours traveling unnecessarily. So, what I suggest is they should get us homes near our campuses because if we are around, our productivity increases. I had a very nice experience when I was at Jimma University.

**Nile:** Staff resident?

**Dr. Neela:** Yes! There was a staff residence when I was in Jimma. There was a building taken by the staff professors. They gave me one room there, and I was secured. This is the most important issue the university should address. Second issue is there is no kind of orientation. Get-togethers are important to meet with different people, to get introduced with ourselves and with the locales as well.

**Nile:** Haven’t you ever had yet?

**Dr. Neela:** Of course, we had, but it is of an Indian by its very nature.

It was a very small one because the number of Indian expatriates is going down. By now, we are not more than twelve. Another thing is that we are dispersed. We are five at BiT; there is one in Zenzelima, agriculture campus, three Selam Campus, EiTex, and one at Peda. Because we are dispersed, we are getting together through personal endeavors; every Friday evening we four meet somewhere. We expect

# ደቀመዛሙርት

ይህ አምድ በዋነኛነት የተማሪዎች ድምፅ እና ተማሪነትን የሚመለከቱ ፅሁፎች ይቀርብበታል

## ችግር የሚያዘጋው በር እና የተማሪወች አስተያየት

በሰው መሆን አላዛር

ሁለተኛ ዓመት የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ት/ት ክፍል

ኮሮና ቫይረስ በአለማችን ከተከሰተ ጊዜ ጀምሮ ሃገራት የየራሳቸውን የቫይረሱን ስርጭት መቆጣጠሪያ መንገድ እና የሚያደርሰውን ጉዳት መቀነሻ እርምጃወችን ወስደዋል በመውሰድ ላይም ናቸው፡፡ሃገራችን ኢትዮጲያም የዚህን ወረርሽኝ ሽርጭት ለመግግታት በርካታ እርምጃወችን በተለያዩ ጊዚያት ወስዳለች፤ አሁንም በመውሰድ ላይ ትገኛለች፡፡

የቫይረሱ ስርጭት የሚገድበው ባለመኖሩ በበሽታው ስጋት ምክንኒያት በርካታ የሚባሉት የሃገራችን ማህበረሰቦች ከስራ ገበታቸው እርቀው የነበሩ ሲሆን በዚሁ ወረርሽኝ ሳቢያ ዩኒቨርሲቲወች ዝግ ሆነው ለወራት ቆይተዋል፡፡ በዚህም በርካታ የሚባሉ ተማሪዎች የተሰላቸ ህይወት እንዲያሳሊፉ ተገደው ቆይተዋል፡፡ ከጥቅምት ወር 2013 ዓ.ም ጀምሮ ዩኒቨርሲቲወች እንደገና ወደ መማር ማስተማር ስራቸው ሲመለሱ በሽታው በዩኒቨርሲቲወች ውስጥ በመዛመት ችግር እነዳይፈጥር ታስቦ የተለያዩ እርምጃወች እየተወሰዱ ይገኛሉ::

ከነዚህ እርምጃወች መካከልም ተማሪወች የአፍና የአፍነጫ መሸፈኛ ለብሰው እንዲንቀሳቀሱ የሚለው አንዱ ሲሆን የተማሪወች የምሽት መግቢያ ሰአት ማሻሻል ድግሞ ሌላኛው እርምጃ ነው፡፡በዚህም መሰረት የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የተማሪወች የመግቢያ ሰአት በፊት ከነበረበት ሶስት ሰአት ወደ አንድ ሰአት ተሸሽሎ በመተግበር ላይ ነው:: ለመሆኑ የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን ለመግታት እና ለመቀነስ ታስቦ የሚዘጋው በር በተማሪወች እይታ ምን ይመስላል፤ተማሪ አሸናፊ ኪዳኔ በዩንቨርሲቲው ውስጥ የሁለተኛ አመት የእንግሊዝኛ ትምህርት ክፍል ተማሪ ነው::

ተማሪ አሸናፊ እንደሚለው የተማሪወች የመግቢያ ሰአት በፊት ከነበረበት ሶስት ሰአት ወደ አንድ ሰአት ተሸሽሎ በመተግበር ላይ መሆኑ በተማሪወች ላይ ችግር እንደሚፈጥር ተናግሮ በዋናነትም በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የምግብ አገለግሎት ተጠቃሚ ያልሆኑ ተማሪዎች በሰአቱ መሻሻል ምክንያት እየተችግሩ መሆናችውን ተናግሯል:: ተማሪ አናንያ ጥላሁን ፣ የአንደኛ አመት ሶሻል ሳይንስ ተማሪ እና ነን ካፊ ተጠቃሚ ስትሆን የተማሪወች የመግቢያ ሰአት በፊት ከነበረበት ሶስት ሰአት ወደ አንድ ሰአት በመሻሻሉ ምክንያት እራት ትበላበት ከነበረበት እና መብላት ከነበረባት ሰአት በፊት እንድትበላ እንዳስገደዳት እና ይህም ለማንበብ በምትጠቀመው የጊዜ ቆይታ ላይ ችግር እንደፈጠረባት አንስታልናለች:: ከዚህ በተጨማሪ ትላለች ተማሪ አናንያ ከግቢ ውጭ አምሽተው ይመጡ የነበሩ ተማሪወች ላይ የሚደርሰው ችግር ከፍተኛ ሊሆን ይችላል:: ይህም ሲባል አምሽተው ይመጡ የነበሩ ተማሪወች የመግቢያ ሰአት እስከ አራት ሰአት ቢሆን ኖሮ ወደ ግቢ የመግባት እድላቸው ሰፊ ነበር ነገር ግን የመግቢያ ሰአቱ ወደ አንድ ሰአት መምጣቱ የተማሪወችን ውጭ የማደር እድል ያሰፋዋል:: ይህ ደግሞ ተማሪወቹን ላላስፈላጊ በሽታ እና ችግር ሊያጋልጣቸው ይችላል ብላለች፡፡

በውኑ የተማሪወች የመግቢያ ሰአት መሻሻሉ ከሚያመጣው መፍትሄ አና ከሚያስከትለው ችግር የቱ ይበልጣል?

## BAHIR DAR UNIVERSITY IN THE EYES OF...

*continued from page 8.*

orientations, gatherings, so when a new expatriate joins the University, we need a high level of orientation in person telling the nature of the University, the structure of the University, who handles the problems of expatriates etc. Everything we are doing here with regard to this is very personal.

**Nile:** Do you mean there is no section to share your problem in the university's structure?

**Dr. Neela:** When we need some information related to Visa, renewal of work permit, and residence permit we contact the External Relation Office and they provide us with the required information. But that is on the basis of our request. But usually when there is no issue, they do not pay a visit. We do not also have a regular meeting, gathering kind of things.

This is what I like to state as a limitation with regard to the relationship between the expatriate and the university, like engaging the expatriates in the university social gatherings. So they know the locals, the different cultures and the different people. For example, I have been here for four years, but I have not seen the Academic Vice President. This is of course because to I get my routines done at department and faculty levels. What I want to emphasis is the need to get introduced and know each other. Our Institute is autonomous, and that could be why I have not yet met the Academic Vice President. I am referring to the new president. Mostly my needs are fulfilled by the Science Advisor, but if we had meeting associations at a higher level frequently, we expatriates would feel more secured, and more friendly as we know more different requirements of the university, like, how we can make the collaboration with others.

**Nile:** You are right. Globalization is all about bringing the best minds together.

**Dr. Neela:** Exactly. I say gatherings play great roles to overcome cultural barriers.

**Nile:** Did not you and friends celebrate the New Year together with the University management? It was viral on the social media, I remember. The University has celebrated it with you for the first time.

**Dr. Neela:** I have never done it here except this year. I have been here for three years it is done only this year.

I think Bahir Dar University has a lot to learn from Jumma University. They do this every year. It is through such events you build your brand, advertise the University for expatriates, international audiences and publics. I hope you should keep on doing it by following the COVID protocol if it happens with you I would highly recommend you to do so.

**Nile:** Anything you'd like to add, about the department and faculty?

**Dr. Neela:** I am very happy with my faculty and the department and the different stakeholders.

I am the only Indian left in my department now. There were many before, but they have left for different reasons. And from the Faculty for Food and Chemical Engineering, I am the only one. I would like to thank my chair, Mr. Solomon Workineh, who is very supportive, not only for the case of office related issues but also for personal cases. Whenever I need help even outside of the city, he is always there for me. I am happy with that. Not only that I am also working for four departments. I am from the Post-harvest Technology and I am handling four people. Although I am over loaded every semester, thanks to the support from my colleagues I am doing it successfully. My friends and colleagues understand the situation very nicely and they support me a lot. So, even you can witness here I have asked these materials because I have a masters scholars and PhDs. That is why I need some office materials, provided I need

# ጤንነት


ለኮቪድ-19 የቤት ውስጥ
ውሸባ እና ክትትል ቅድመ ሁኔታዎች
የኮቪድ-19
1• በላቦራቶሪ የተረጋገጠ የኮቪድ-19 ፖዘቲቭ ውጤት


ኮቪድ-19 የቤት ውስጥ ውሸባ
እና ክትትል 6 ቅድመ ሁኔታዎች
2 • እድሜያቸው ከ60 ዓመት በታች የሆኑ
ለበለጠ መረጃ በነፃ
የስልክ መስመር
8335 ወይም 952 ይደውሉ


ኮቪድ-19 የቤት ውስጥ ውሸባ
እና ክትትል 6 ቅድመ ሁኔታዎች
3 • የኮቪድ-19 ምልክት የሌላቸውና መጠነኛ
ምልክቶች ያለባቸው
ለበለጠ መረጃ በነፃ
የስልክ መስመር
8335 ወይም 952 ይደውሉ


ኮቪድ-19 የቤት ውስጥ ውሸባ
እና ክትትል 6 ቅድመ ሁኔታዎች
የረጅም ጊዜ ክትትል የሚፈልጉ እንደ ደም ግፊት፣ ስኳር ህመም፣
አስም እና የመሳሰሉት በሽታዎች ያሉባቸው ህመምተኞች ከሆኑ
በሕክምና ክትትል ስር ያሉ እና ያልተባባሱ ከሆነ


ኮቪድ-19 የቤት ውስጥ ውሸባ
እና ክትትል 6 ቅድመ ሁኔታዎች
5. የህክምና ባለሞያ በቤት ውስጥ ይቆዩ
ብለው ሲወስኑ


ኳንዳናገለግልዎ
ማለካዎን ያድርጉ
ኮቪድ-19 የቤት ውስጥ ውሸባ እና
ክትትል 6 ቅድመ ሁኔታዎች
6. ሥር የሰደደ የመተንፈሻ አካል የጤና ችግር የሌለባቸው
ለበለጠ መረጃ በነፃ
የስልክ መስመር
8335 ወይም 952 ይደውሉ


መዘናጋት ብዙዎችን እያሳጣን ነው!

# ኪነጥበብ እና ባህል




በአስቴር ሙሉ(ዶ/ር)
የባህልጥናት ት/ት ክፍል ባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ

ባለቤቴ ማህፀነ መልካም የሚሏት አይነት ሴት ናት:: የአንድ ወንድ የሁለት ሴቶች በአጠቃላይ የሶስት ቆንጆ ቆንጆ ልጆች አባት አድርጋኛለች:: የምገልፅበት ቃላት እስኪቸግረኝ ድረስ ልጆቼን በጣም ነው የምወዳቸው:: ያሳሱኛል:: ከዚያ በላይ በሰፈሬም ሆነ በስራ ቦታዬ አንቱ ተብዬ ለመኖሬ ምክንያቶቼ ናቸው:: በእርግጥ ለክብሩ ለክብሩ ትዳሬም ቢሆን የራሱን ሚና እየተጫወተ እንደሆነ አልረሳሁትም:: በሰፈር ውስጥ ለሚመረጥ የኮሚቴ አባልነት እስከመስሪያ ቤት ሹመት ድረስ ባለትዳር፣ የተረጋጋ የሚሉ መስፈርቶች ዋጋ አሰጥተውኛል:: የትዳሬ ነገር ግን ውጪ ውጪን ይህንን ይምሰል እንጅ ውስጡ ለቁስ ከሆነ ሰነባብቷል::

ባለቤቴ እንደምትለው ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ሴቶችን ሳናግር የማሳየው ትህትና ያበሽቃታል:: አንድ ቀን ‹‹ይህንን አይነት ትህትና ማሳየት ያለብህ ለእኔ ነው፣ለእኔ ማታሳየውን ባህርይ ለሌሎች የምታሳይ ድብቅ ባህርይ ቢኖርህ›› ነው ብላኝ ትልቅ ጭቅጭቅ ውስጥ ገባን:: ይህንን ተከትሎ ይመስለኛል ባለቤቴ ለፍቅር ግንኙነት ያላት ፍላጎት ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚችል ሁኔታ ጠፋ:: እኔ ግን ይህ እንዲሆን አልሻም:: ምን ሆንሽ ስላት? በደፈናው ‹‹አንተ ምን አለብህ?›› ‹‹ እኔ ይደክመኛል››፤:: የሚል መልስ ትሰጠኛለች::

በእርግጥ ሊደክማት እንደሚችል እገምታለሁ:: በአንድ በኩል የመስሪያ ቤት ስራ አለባት፣በሌላ በኩል በቤታችን ውስጥ ሰራተኛ ከሚኖርበት ጊዜ ያይኖርበት ይበዛልና የቤት ውስጥ ስራ ትሰራለች:: እኔ ጥሎብኝ የኩሽና ስራ አልወድም፤አልችልምም:: በዚህ የተነሳ ብቻዋን ነው የምትደክመው፣ ሶስት ልጅ፣አንድ አባወራ በቀለብና በሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች ሁሉ መንከባከብ ቀላል ጉዳይ አይደለም:: ይህ ያላነሳት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪዋን በስነፅሁፍ ለመያዝ ፣ትማራለች:: ታዲያ አሁን ላይ የመመረቂያ ፅሁፏን እየፃፈች ነውና የሌሊቱን አብዛኛውን ክፍል ሳትተኛ ኮምፒውተር ላይ አፍጠጣነው የምታድረው:: በእውነት በዚህ በዚህ እንኳን በጣም ጠንካራ ናት:: ግን ትዳራችንስ፣ ምነው የግብረ ስጋ ግንኙነት በትዳር ውስጥ ቁልፍ ጉዳይ አይደለምን? ምነው ስታነባቸው ከምትውላቸው የልቦለድ ሆነ የቲወሪ መፃህፍት ይህንን እውነት የሚገልፅላት አንድ እንኳን ጠፋ?፣ይህንን ለመረዳትስ እንዴት አቃታት? ለብዙ ቀናት በእነዚህ ጥያቄዎች መብሰልሰል ስራዬ ሆነ::

ይህንን ትረዳ ዘንድ ስራዬ ብዬ መፅሀፍቶችን ፈላልጌ እንድታነብ ሰጠኋት፣ ‹‹አንተ አለሙ ላይ ነህ›› ብላ ተሳለቀችብኝ:: ከድካም ውጪ ምክንያት ይኖራት ይሆን ብዬ ለመረዳት ብዙ ጥረት አደረግሁ:: ነገር ግን የሚሻሻል ነገር አልሆነም:: ከቀን ወደ ቀን በአንድ ቤት ውስጥ እየኖርን በተለያየ ቤት እንደሚኖር ሰው ሆንን፤ አንድ አልጋ እየተኛን የማንተያይ ጀርባ ተሰጣጥተን የምናድር ሰዎች ሆነን አረፍነው:: እንዲያውም ይባስህ ብላ የመኝታ ክፍሏን ለወጠች:: እኔም በአንድ ሰፊ መኝታ ቤት ውስጥ ለብቻዬ ሰፊ አልጋ ላይ ስገላበጥ፣አለዚያ ደግሞ እድሜ በደህና ቀን ላስገባሁት ‹‹ዋይ›› ‹‹ፋይ›› የኢንተርኔት አገልግሎት ላፕ ቶፕ ኮምፒውተሬን ከፍቼ ሳነብ፣እንዲያም ስል ከጓደኞቼ ጋር ‹‹ኦን ላይን››፣ ‹‹ ቻት›› ሳደርግ ሌሊቱን አሳልፋለሁ::

ይህ በእንዲህ እንዳለ ታዲያ አንድ ቀን ሌሊት ላፕቶፕ ኮምፒውተሬን ከፍቼ በፌስቡክ ገፅ ከአንድ አሜሪካን ሀገር ከሚኖር የድሮ ጓደኛዬ ጋር እያወራሁ ሳለ ሉሲት አሰፋ የሚል ስም ካላት ሴት ‹‹friend request›› /‹‹የጓደኛ እንሁን›› ጥያቄ መጣልኝ::

እሽም፣ እምቢም ከማለቴ በፊት የጠያቂዬን ማንነት ለማየት ፕሮፋይሏን ከፈትሁ:: ሴት ናት፣ (በእርግጥ ሴት መሆኗን ፕሮፋይል ፒክቸሯን በማየት አውቄያለሁ):: wአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማረች ናት፣ ዕድሜዋ ሰላሳ ሁለት፤ከዚህ በላይ መረጃ የላትም:: ማን ያውቃል ይህ ራሱ ውሸት ሊሆን ይቸላል:: የፌስ ቡክ ነገር!

የሆነው ሆኖ የጓደኝነት ጥያቄዋን ተቀበልሁት:: በልማዴ ብዙ ጊዜ እንዲህ አይደለሁም:: ለማላውቀው ሰው የጓደኝነት ጥያቄ አልልክም:: ከማላውቀውም አልቀበልም:: ዛሬ ግን ተቀበልሁ::

እውነት ለመናገር በሌሊት የመጣ ጥያቄ መሆኑም አስገርሞኛል:: ምናልባት በሌሊት ከሴት የመጣው ጥያቄ ትንሽዬ ሀጢያት የመስራት ፍላጎት በውስጤ ፈጥሮ ይሆናል ጥያቄውን የተቀበልሁት:: ጠያቂዬ ወንድ ቢሆን ‹‹እቀበለው ነበር?›› ብዬ ራሴን ጠይቄያለሁ:: መልሱን ከመስጠቴ በፊት ግን ‹‹ሀይ›› የሚል ሰላምታ ከዚያኛው ጫፍ ስለመጣልኝ:: መልሱን ረሳሁት::

‹‹ሀይ›› አልኩኝ:: ወሬያችን ቀጠለ::

‹‹አትተኛም፣በዚህ ሌሊት ምን ትሰራለህ?››

‹‹አንቺ ምን ትሰሪያለሽ?››

‹‹አልነግርህም?››

‹‹እባክሽን!›› ሳላውቀው ልምምጥ ገባሁ::

‹‹እኔ እኮ ነኝ ቀድሜ የጠየቅሁህ፣››

‹‹ እሽ እያነበብሁ ነበር››

‹‹ምን? ምንድን ነው የምታነበው?፣ተማሪ ነህ? ስንተኛ ክፍል?፣ነው ዩኒቨርሲቲ?›› በጥያቄ ላይ

ጥያቄ አዘነበችብኝ::

‹‹ ሠራተኛ ነኝ?›› ታዲያ እንደሱ አትልም:: አስቀድመህ››

‹‹አልኩ እኮ፣ተማሪ ብሆን ሠራተኛ አንቺን ምን ይነካሻል››

‹‹ይነካኛል፣አግብተሀል፣

‹‹አዎ››

‹‹ ታዲያ፣ ሚስትህ እዚያ ነገር ላይ እንዴት ናት?

‹‹ማለት?››

‹‹ምን ማለት አለው፣አሪፍ ናት አይደለችም?››

‹‹ባትሆንስ?››

‹‹ካልሆነች አሪፎች አለን!››

በጣም ደነገጥሁ፣በጣም በሸቅሁ . . በጣም . . . ድብልቅ. . . ልቅ. . . ልቅ. . . ያለ ስሜት ተሰማኝ:: ኮምፒውተሩን ከደንሁት:: ልክ ቤት ዘግቶ እንደመውጣት ዮሴፍ የፈርኦኑ ሚስት አብሯት እንዲተኛ ስትጎትተው ነጥቋት እንደወጣው አይነት:: ልክ እንደዚያ ፔጁን ሳይሆን የዘጋሁት ኮምፒውተሩን ከደንሁት ከመገተት እንደማምለጥ ነጥቆ እንደመሮጥ::

ነገር ግን እኔ ዮሴፍን አይደለሁም:: ከኮምፒውተሩ እይታ ብወጣም ምልልሳችን ከሀሳቤ አልወጣ አለኝ:: ምልልሳችንን ከመጀመሪያ ጀምሮ በምናቤ አሰብሁት፤ደሜ ሲሞቅ ተሰማኝ:: ነገርዬየ ሲወጣጠር ታወቀኝ:: ራሴን ለመግዛት ብዬ ሌላ አሳብ ለማሰብ ሞከርሁ:: ብዙ አልዘለቅሁም:: ሚስትህ እዚያ ነገር ላይ እንዴት ናት? . . . አሪፍ ናት? ካልሆነች አሪፎች አለን!›› የሚለው ንግግር ውስጥ እመለሳለሁ::

በ‹‹ላድርገው ልተወው›› ሀሳብ ለጥቂት ደቂቃዎች ምናልባትም ሰከንዶች ስወዛገብ ከቆየሁ በኋላ ኮምፒውተሩን ከፈትሁት:: ከፈትሁትና ወደ ምልልሱ ሄድሁ:: ከዚያ ጫፍ ያለችው ሴት መስመር አሁንም ‹‹አክቲቭ›› ነው:: ምን እንደምል እንኳን ሳላስብበት ‹‹ እና

ወደ ገፅ 6 ዞሯል

# ከፍተኛ ትምህርት... ከገፅ 7 የቀጠለ


የሚዳብርበት፣ የሚበለፅግበት ትልቅ ተቋም ነው:: ይህንንም ቁልፍ ተግባር ለማከናወን መማር ማስተማርና ምርምርን በትጋት ሊከውኑ የሚችሉ የላቀ አስተሳሰብና አሠራር ያላቸው ሠዎች መገኛ ተቋም ነው ተብሎ ይታመናል፤ ነውም ጭምር::

በተለያዩ አህጉራት ያሉ ዩኒቨርሲቲዎችን ስንመለከት አዳዲስ ግኝቶች፣ አሠራሮች፣ ፍልስፍናዎች የሚፈልቁት ከነዚህ ተቋማት ነው:: እነዚህ ተቋማት የዕውቀት መፍለቂያ፣ የአዳዲስ ግኝቶች መነሻ፣ ሳሳቦች የሚያድጉበት ባህል የሚበለጽግበት ተቋማት ናቸው:: ለምሳሌ አንድ ማሳያ እንኳን ብንመለከት በአሁኑ ወቅት በአለማችን ለሰው ልጅ የመኖር ስጋት የሆነውን ወረርሽኝ (COVID-19 Pandemic) ክትባትን በማግኘት ዙሪያ ብሪታኒያ የሚገኘው University of Oxford ተመራማሪዎችን ጥረትና ግኝት ማየት በቂ ነው:: ከልፋታቸውም የተነሳ AstraZeneca vaccine በማግኘት ለአለም አበርክተዋል:: ክትባቱም በአሁኑ ሰአት በተለያዩ ሃገራት እየተሰጠ ይገኛል:: ከዚህም በተጨማሪ እንደ Johns Hopkins University ያሉ ዩኒቨርስቲዎችም ለዚህ አለምን ላስቸገረ ወረርሽኝ መፍትሄ ለመሆን ደፋ ቀና እያሉ ይገኛሉ:: ለምን ቢባል ዩኒቨርሲቲዎች የምርምር ማዕከላት፣ የዕውቀት መፍለቂያና ማበልፀጊያ ተቋማትና መካነ አእምሮ ስለሆኑ ነው::

ስለሆነም ዩኒቨርሲቲዎች ይህን የተጣለባቸውን ትልቅ ሃላፊነት ለመወጣት የቁሳዊ አካባቢያቸውም ሆነ የስነ-ልቡናዊ ዝግጁነታቸውን ሁልጊዜ መፈተሽ ይኖርባቸዋል:: ለምን ቢባል አንድ ገበሬ (አርሶ አደር) ዘር ዘርቶ ምርት አምርቶ ከመሰብሰቡ በፊት ዘሩ የሚያርፍበትን መሬት በደንብ ያዘጋጃል፤ አልሞ ያርሳል፤ መሬቱን ያለሰልሳል፣ መሬቱ ለዘር መዘጋጀቱን ካረጋገጠ ዘሩን ይዘራል:: ከዛም ሰላሳ፣ ስልሳና መቶ ያፈራለታል:: ተቋማትም የስራ ስምሪት ከመስጠታቸው በፊት በተቻለ ዓቅም ሰራተኛው ጥሩ አምራች እንዲሆን የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው:: እርግጠኛ ሲሆኑ ስራን ቆጥረው ይሰጣሉ ውጤቱንም በቀላሉ ይሰበስባሉ::

የተቋማትናየተቋማትአመራሮችሚና

ተቋማትና የተቋማት አመራሮች ዩኒቨርስቲዎች የጥሩ መኖሪያ ቤት ( Good Home) ምሳሌ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው:: ቢሮዎች፣ መስሪያ አካባቢዎች፣ ግቢው ምን ያህል ለመማር ማስተማርና ምርምር ስራዎች ምቹ መሆናቸውን ማረጋገጥ ግድ ይላቸዋል::




መምህራን፣ ተመራማሪዎች፣መማር ማስተማሩንና ምርምሩን የሚደግፉ የተለያዩ ሠራተኞች ምቹ የሥራ አካባቢ ተፈጥሮላቸዋል ወይ ብሎ ፍተሻ ማካሄድ የተቋሙ ተቀዳሚ ስራ መሆን ይኖርበታል:: ቢሮዎች፣ የመማሪያ ክፍሎች፣ የቤተ-ሙከራ ቤቶች፣ ቤተ መፃህፍት፥ የማንበቢያ ቦታዎች ፅዱ፣ ማራኪ፣ ህሊናን ሡብሰብ አድርገው መያዝ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አንዱ ቁልፍ ተግባራቸው መሆኑን ማሰብ ይኖርባቸዋል:: በተጨማሪም በስራ አካባቢዎች ሥራን የሚያቀላጥፉ፥ የሰውን ልጅ ድካም የሚቀንሱ፥ መማር ማስተማሩን፥ ምርምሩን፥ ማህበረሰብ አገልግሎቱን የሚደግፉ ቴክኖሎጅዎች መኖራቸውን ማረጋገጥና ክፍተቱት መሙላት ሌላኛው ሃላፊነታቸው ነው::

በተለይ በተለይ ደግሞ ከስራ ድካም ጋር በተያያዘ ቡና፣ ሻይ፣ ውሃ ለመጠጣት አንድ ሰው ቢፈልግ ለአንዲት ስኒ ቡና ከቢሮው ወጥቶ፣ ብዙ ርቀት ተጉዞ ፣ጊዜ አቃጥሎ፣ እንዲያዉም ለሻይ ወጥቶ በዛው ጠፍቶ የሚቀር ብዙ ሰው አለና መሰል መሰናክል ማስቀረት እንዲህ ያሉ አገልግሎቶችን በቢሮዎች አካባቢ ማቅረብ መቻል እንዲሁም የቢሮዎችን አደረጃጀት በዚህ መልኩ ማዘጋጀት መቻል አንዱ ትልቅ የአስተዳደርና አመራር ጥበብ ነው::

ለትምህርት በተለያዩ የውጭ ሃገራት በሄድንበት ጊዜ በየዩኒቨርስቲው ያየነው አብይ ጉዳይና ለኛም እንደጥሩ ልምድ መውሰድ የምንችለው ነገር ቢኖር መምህራን ረዘም ያለ ቀጠሮ ይዘው እየተጫወቱ ለማውራት ወይም የምሳ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ለሻይ ለቡና ብለው ከቢሮአቸው ርቀው አይሄዱም :: ይልቁንስ በመምህራንና ሰራተኞች ቢሮ ኣካባቢ ራሳቸው መምህራን በቀላሉ አዘጋጅተው ሊገለገሉባቸው የሚችሉበት ምቹ የስራ አካባቢ ስለተፈጠረላቸው እዛው ቢሮአቸው አካባቢ ሁኔታዎች ተመቻችቶላቸው የሻይና የቡና አገልግሎቱን ራሳቸው እያዘጋጁ ስራቸውን ባግባቡ ይሰራሉ:: የሽንት ቤትም ሆነ ሌሎች አገልግሎቶችም እንዲሁ በደንብ ጥራታቸውን ጠብቀው አገልግሎት ይሰጣሉ:: እንዴያውም ሽንት ቤቶቻቸው ምን ያህል ጽዱና ማራኪ ከመሆናቸው የተነሳ የደከመ ሰው የሚያርፍበት ቦታም ጭምር በማሰብ የተዘጋጁ ስለሆነ መጠሪያ ስማቸው ራሱ ተቀይሮ ''Rest Room'' ተብለው ይጠራሉ::

ባጠቃላይ ቢሮዎች፣ ጠረንጴዛዎች፣ የምንቀመጥበት ወንበር፣ የመፃህፍት መደርደሪያ ሽልፎች ስታንዳርዳቸውን ያሟሉ ሆነው ተሟልተው የተቋሙ ሰራተኛ ሥራችዉን ያለአንዳች ድካምና ማንጐራጐር እንዲሰሩ ማስቻል የተቋሙን ብቃትና የአመራሩን ጥራት ላቅ ያደርገዋል:: የመምህራን ቢሮ ተማሪዎችን ለማማከርና የምርምር ስራ ለማካሄድ ምቹ መሆኑን ማረጋገጥ አንዱ የብቃት ማረጋገጫ አመልካች እንዲሆን መስራት ያስፈልጋል:: የመማሪያ ክፍሎች (Classrooms) ምን ያህል ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ ናቸው? የክፍሎች አደረጃጀት፣ ነፋሻማነት (ventilation)፣ ሶኬቶች፣ ጥቁር ሰሌዳው፣ የ LCD Projectorና ማስቀመጫዎች የመሳሰሉት ግብዓቶች ምን ያህል ተልዕኮዎቻችን ለማሳካት ያግዛሉ? የቤተ-ሙከራዎችና ቤተመጻህፍት ምን ያህል በቁሳቁስ፣ በኬሚካል፣ በመፃህፍት፣ የተሟሉ ናቸው? ቤተ-መፃህፍቶቻችን ለመምህራን፣ ሰራተኞች እንዲሁም ለተማሪዎች ምን ያህል ምቹ ናቸው? አንብቡብኝ፣ አትውጡብኝ ይላሉ? ተመራመሩብኝስ ይላሉ? እነዚህን በርካታ ጥያቄዎችን አንስተን ስንጠይቅና ጥያቄዎቻችን አጥጋቢ መልስ ካገኙ እውነትም ዩኒቨርሲቲዎቻችንን ከቤታችን ውጭ የሆኑ ቤታችን (A school as home away from home) ሆነዋል ማለት ነው:: ይህ ሲደማደም ተቋሙ የጥሩ መኖሪያ ቤት ምሳሌ ሆኗል ማለት ነው::

የሰው ልጅ ቁሳዊ ፍላጎት ብቻ የለዉም:: የሰው ልጅ ቁሳዊ ፍላጎት ብቻ ተሟልቶለት ውጤታማ ሰራተኛ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም:: ማህበራዊ እንስሳ እንደመሆኑ መጠን የስነልቡናም ይሁን ማህበራዊ ፍላጎቱ እንዲሟሉለት ይፈልጋል:: ስለሆነም በሚሰራበት አካባቢ በፋካልቲ፣ መምህራንና ሰራተኞች፣ በተማሪዎች መካከል ያለው የእርስ በእርስ መስተጋብሩ ጎልቶ መውጣት አለበት:: ይህንንም ለማሳካት የቡድን ስራዎች፣ ምርምሮችን ማህበራዊ ፋይዳ ያላቸው ግንኙነቶች እንዲኖሩት ስልት መቀየስ ያስፍልጋል:: የጉብኝት መርሃ ግብሮችን ፣ የስፖርት ክበባትን፣ የተለያዩ ባህላትን (Rituals) ማዘጋጀትና የዩኒቨርስቲውን ማህበረሰብ እንዲሳተፍ ማድረግ ትልቅ የስዕብና መገንቢያ መንገድ ነው:: ይሄም አንዱና ዋነኛው የጥሩ መኖሪያ ቤት ምሳሌ መሆን ነው::

ይህ ጽሁፍ ሲጠቃለል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በተለይም ደግሞ ዩኒቨርስቲዎች ያለባችውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና፣ ባህላዊ ዕድገት ሃላፊነት በትጋትና በብቃት ለመወጣት ያስችላቸው ዘንድ በጥሩ አለት ላይ የተገነቡ መሆን አለባቸው:: የመልካም ቤተሰብ ምሳሌ ሆነው መዋቀር ይኖርባቸዋል:: ለዚህም የተቋሙ አመራሮች በዕውቅት ላይ የተመሰረተ አመራር መስጠት፣ አቅጣጫ ማሳየት፣ መምራት፣ ሰርቶ ማሰራት፣ ይጠበቅባቸዋል:: መምህራኑም ሰራተኛውም ራሱን ለተልዕኮ ብቁ ማድረግ፣ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል የተጣለበትን ሃላፊነት መወጣት፣ ከግላዊ ጥቅምና ፍላጎት ራስን ማራቅ፣ በምክንያት ላይ የተመሰረተ ሃሳብ (Critics) ማቅረብ፣ የቡድንና የተናጥል ስራዎችን በታላቅ ሃላፊነት መወጣት ባጠቃላይ የሚታዩ ችግሮችን በምርምር መፍታት ይጠበቅባቸዋል::

=========== ይቆየን

=====================

# የሳይንስ ጥግ

ይህ አምድ ሳይንስ እና ቴክኖሎጅ ነክ የሆኑ ፅሁፎች ይቀርብበታል

## በስርዓተ-ምግብ (Nutrition) ዙሪያ አውደ-ጥናት ተካሄደ

በሙሉጉጃም አንዱዓለም



የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በከፊል ከውይይት በኋላ

የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት ስር የሚገኘው ኬሚካልና ምግብ ምህንድስና ፋኩልቲ «Applied Human Nutrition» ትምህርት ክፍል ከተለያዩ የአገር ውስጥ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ከመጋቢት 20 እስከ 21/2012 በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቱ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በስርዓተ-ምግብ (Nutrition) ዙሪያ አውደ-ጥናት አካሄደ፡፡

መርሃ ግብሩ በይፋ መጀመሩን ያበሰሩት የፋኩልቲው ዲን ዶ/ር መታደል ካሳሁን ዲኑ ከአሁን በፊት በዚህ አጀንዳ የመወያየት ልምዱ ብዙ እንዳልሆነ አስገንዝበው ከሳይንሱ ጀምሮ እስከ አያያዙና አጠቃቀሙ ድረስ ያለውን የስርዓተ-ምግብ (Nutrition) ምንነት የሚዳስስበት መድረክ እንዲሆን ተመኝተዋል፡፡

የትምህርት ክፍሉ ተጠሪ ዶ/ር መስፍን ወጋየሁ በበኩላቸው የዓውደ ጥናቱ ዋና ዓላማ በስርዓተ-ምግብ (Nutrition) ዙሪያ ሁሉም የሚመለከተው አካል የነቃ ተሳትፎ በማበርከት የአንዱን ልምድ ለሌላው በማጋራት የእውቀት ሽግግር ለማድረግና ለወደፊት መሬት የነካ ስራ ለመስራት የትኩረት አቅጣጫዎች የሚለዩበት እንዲሆን ታልሞ መዘጋጀቱን አስገንዝበዋል፡፡

በመርሃ ግብሩ የተለያዩ ፅሁፎች የቀረቡ ሲሆን በቀረቡት ፅሁፎች በቀረቡ በርካታ ጥያቄዎችም መነሻነት ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡

በአውደ ጥናቱ ደብረ ማርቆስ፣አዲስ አበባ ሳይንስና ዋሳ፣ወለጋ፣ወልቂጤ፣አርሲ፣ጅጅጋ እና ኮተቤ ሜትሮፖሊታን ዩኒቨርሲቲዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡

ከመድረክ ውይይት ጎን ለጎን በፋካልቲው ስር ያሉ ቤተ-ሙከራዎች ተጎብኝተዋል፤የእንግዶችን ቀልብ የሳቡና ይበል የሚያሰኝ ተግባር የሚከናዎንባቸው፡- Nutrition Skill Laboratory, Documentations of the Applied Human Nutrition program, Food Process Laboratories እና Business and Technology Incubation Center (የቢዝነስና ቴክኖሎጂ ኢንኩቤሽን ማዕከል) ሲሆኑ ተማሪዎች ተግባር ተኮር ትምህርታቸውን የሚያካሂዱባቸው መሆኑን ተገልጿል፡፡

ለፋኩልቲው የተለያዩ ድጋፍ የሚያደርገው Jhpiego Growth through Nutrition Activityበተሰኘው ፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፍ በመሰራት ላይ ያለው "Model Smart Class Room" ሌላው የጉብኝቱ አካል መሆኑና ወቅቱን ባማከለ መልኩ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ መስፋፋትን በሚቀንስ መልኩ ተዘጋጅቶ ንፁህ አየር ለማግኘት የሚያስችሉ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን በውስጡ የያዘ ክፍል መሆኑን ከምልከታው መገንዘብ ተችሏል፡፡


የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች በቴክኖሎጅ ተቋም መሰብሰቢያ አዳራሽ

# ስብጥር

ይህ አምድ በሌሎች አምዶች ያልተስተናገዱ ልዩ ልዩ ፅሁፎች ይቀርብበታል

## ‘አቶ አሊ’… ከገፅ 15 የቀጠለ

ብሎኮች ሌላ ምንም የለም ባዶ ሜዳ ነፋሱ አያስቀምጥም ነበር ያንጊዜ ፔዳ ኑሯችን በግቢ ውስጥ ጥሩ ነበር፡፡ ሰራተኛ ይንከባከበን ነበር፡፡ ከሰራተኞች ጋር ከመምህሩም ጋር ጥሩ ግንኙነት ነበረን ያበረታቱን ነበር አብረን በጋራ እንሰራ ነበር፡፡ ጫካ ውስጥ መሆናችን አይሰማንም ነበር 1970 ዓ/ም ላይ እኛ ተመርቀን ስንወጣ ሌሎች 100 ተማሪዎች ተመልምለው መጡ 1ኛ አመት ተጀመረ፡፡ አሁን ያየነው ከምግብ ቤቱ ፊት ለፊት የሴቶች ማደሪያ የዛኔ የሳይንስ ተማሪዎች ተብለው በዲፖሎማ የሚሰለጥኑ ልጆች ነበሩ፡፡ በዛን ወቅት ለማበረታቻ 25 ሳንቲም እየተከፈለን ከኦዲተሪዬም ምግብ ቤት ድረስ ያሉትን እድሜ ጠገብ ዛፎችን እኛ ነበር የተከልናቸው አሁን ሳያቸው ግርምት ፈጥረውብኛል ሳቅ… ያኔ ከዛፎች በተጨማሪ ጎመን እንተክል ነበር እንደዚህ ስናደርግ ጭንቀትን እናስወግድ ነበር፡፡ አሁን ያሉ ተማሪዎችም የተለያዩ አትክልቶችን መትከልና ወደተፈጥሮ መመለስና አካባቢያቸውን ማስዋብ ቢችሉ መልካም ነው፡፡ አንድ ተማሪ አንድ ችግኝ ተክሎ እንዲወጣ ቢደረግ ያ ተማሪ ወደፊት ተቋሙን ይወደዋል፡፡

**ናይል፡-** ከባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ ከተመረቁ በኋላ የመማር እድል ገጥሞዎታል?

**አቶ አሊ፡-** የመማር ፍላጎት ነበረኝ ያን ጊዜ ዝም ብሎ ዘሎ ዩኒቨርሲቲ መግባት ከባድ ነበር፡፡ ብዙ መስፈርቶች ነበሩት ከዚያም በተጨማሪ ጅማ መምህራን ማሰልጠኛ 1971 — 1973 ዓ/ም ድረስ ካስተማርኩ በኋላ የማስተማር ስራዬን ትቼ በሌላ የስራ ዘርፍ ተሰማራሁ በኋላም ወደ ማዕከላዊ ‘ኢስፓኮ’ ሂደህ ትሰራለህ መቀበል ደግሞ ግዴታህ ነው፡፡ ስራውም ‘ሰርቶ አደር’ የሚባል የፓርቲው ልሳን 11 አመት መምሪያ ሀላፊ ሆኜ ሰርቻለሁ፤ የኤርትራም ወኪል ሁኜ ሰርቻለሁ ፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪዬን ‘በፔዳጎጂ’ ሳይንስበ1970 ዓ/ም ከባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ ካገኘሁ በኋላ ሁለተኛ ዲግሪዬን ‘በስፔሻሊስት’ ትምህርት ከ1983 ዓ/ም በኋላ ነው ያገኘሁት፡፡

**ናይል፡-** በውጭ ሀገር ቆይታ ያገኙትን መልካም ተሞክሮ ቢያካፍሉን

**አቶ አሊ፡-** ቀደም ብዬ የማስተማሩን ስራ ትቼ ወደ ልሳን ዝግጅት ገብቻለሁ በልሳን ዝግጅት ሁሉንም የምስራቅ አውሮፓ ሀገሮች ዞሬያለሁ፣ በቆታዬም ከልሳን መጽሄት እና ጋዜጣ ዝግጅት ጋር የተያያዙ አጫጭር ቆይታዎች ነበሩኝ፡፡ የሀገሪቱ ታላላቅ ባለስልጣን ወደ ውጭ ሲወጡ የተለያዩ አፍሪካ ሀገሮች እና አውሮፓ ሀገሮች በተደጋጋሚ የመሄድ አጋጣሚ ነበረኝ፡፡ ከሶሻሊስት ሀገሮች ኮርሶችን እና ተሞክሮዎችን ወስጃለሁ፡፡

**ናይል፡-** ለተማሪው ተሳትፎ ትኩረት የሰጠ በነጻ ማሰብን የሚያበረታታ ዜጋ ማብቃት የሚችል ተቋም እንዴት መፍጠር ይቻላል ብለው ያምናሉ?


**አቶ አሊ፡-** ቀደም ሲል የትምህርት ቤቱ ታላቅ ሰው ማነው ሲባል አስተማሪ ነው እየተባለ ነው የመጣነው ወደ መማር ማስተማሩ ስንመጣ ግን ታላቅ ሰው የሚባለው መምህሩ አልነበረም፡፡ ተማሪው ነበር፣ በመሆኑም አንድ ጥሩ ተቋም ለመመስረት ትኩረት ተሰጥቶ ከታች ተማሪው ላይ መሰራት አለበት፡፡ ነገር ግን ባለፉት 3 አስርት አመታት የነበረው ስርዓተ ትምህርት ቢታይ በአብዛኛው የተወረሱ ናቸው፡፡

ከፈረንሳይ ሀገር ያመጣነው ስርዓተ ትምህርት ለተወሰነ ጊዜ ሰራ ‘ፍሬንች ሲስተም’ የሚባለው በሀይለስላሴ ጊዜ ተለወጠ ከዛ ወደ እንግሊዝ ሄድን ‘ብሪቲሽ ሲስተም’ መጣ ‘ማትሪኩሌሽን’ እሱም የተወሰነ ጊዜ ሰራ ኢትዮጵያ አፈር ላይ መልመድ አልቻለም፡፡

ከዚያ ወደ አሜሪካ ሲስተም ገባን አጥቁር ‘ኦብጀክቲቭ’ ጥያቄ እሱም በተወሰነ የመጣ ነው ለነሱ ሰርቶ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ተማሪ ተኮር የሆነ ተቋም የሰው ሀይል የሚያፈራ ተቋም እንመስርት ከተባለ መነሳት ያለብን ከትምህርት ፖሊሲው ነው፡፡

ስለዚህ ፖሊሲው የተስተካከለ መሬት የረገጠ ነው ወይ የሚለው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ አሁን ተግባራዊ ሊሆን የተዘጋጀው የትምህርት ፍኖተ ካርታ ካሁን በፊት በስርዓተ ትምህርቱ ላይ የሚታዩ ጉድለቶችን አይተው የተዘጋጀ ይመስለኛል፡፡

ወደ ራሳችን እንመለስ ከችግር እንነሳ ወደ ሀገር ስንመጣ ብዙ ብሂሎች አሉን በጣም አስተማሪ የእምነት ትምህርቶቻችን ይሰጡት የነበሩት እና ያወጡት የነበረ በስነ ምግባር የታነጸ ዜጋ መልካም ተሞክሮ ነበር፡፡ የተለያዩ መድሀኒቶችን የሚቀምሙ ባለሙያዎች እኮ ነበሩ ድሮ አባቶቻችን የጻፏቸው መጽሀፍቶች እየተለቀሙ ጀርመን ሙዚዬም ገብተዋል፡፡ ጀርመኖች ዛሬ በዶክትሬት ዲግሪ ደረጃ ግዕዝ እያስተማሩ ነው፡፡




እነዚያን መጽሀፍት ለማስተርጎም የመድሀኒት መጽሀፍቶች የፍልስፍና መጽሀፍቶች እነዚያ ሰዎች የጻፏቸው ሊጠቀሙባቸው ይፈልጋሉ ለዚያም ነው የግዕዝ ቋንቋ ወሎ ዩኒቨርሲቲ የጀመረውነገር አለ ሲባል ሰምቻለሁ፡

ወደ ሀገራችን ተመለስን ማለት ይህ ነው፡፡ ችግር ፈች ስንል መስኖን አስፋፍቶ ህብረተሰቡንና ራሱን የሚመግብ ካልሆነ የምናወጣው ዜጋ ምን ይፈይድልናል አሁን የተዘጋጀው የትምህርት ፍኖተ ካርታ ይህንን የሚያበረታታ ወደ ራስ መመለስን በጥልቀት ያየ ይመስለኛል፡፡

**ናይል፡-** ስለትውልድ ቦታዎ የተማሪነት ህይወትዎ ቢያጫውቱን?

አቶ አሊ፡- የወሎ ጠቅላይ ግዛት ደሴ ዙሪያ አውራጃ ሩጋ በምትባል በጣም ለምለም ለደሰ ከተማ የወተ ት አቅርቦት ምንጭ በሆነች መንደር ነው የተወለድኩት፡፡ ወተት እጠጣሁ ነው ያደኩት …ሳቅ… ትምህርዮን እዛው ሩጋ ትምህርት ቤት ነው የተማርኩት፡፡ ስያሜውንም ያገኘው በወቅቱ ጣሊያን በመጣ ጊዜ ለምለም ከመሆኗ የተነሳ ‘ቶሪ’ የሚባል የጣሊያን ‘ኮማንደር’ ያችን ቦታ ይዟ የተሰራ የኮማንደር ቶሪ የሚባል የመኖሪያ ቤት ነበር፡፡ በ1952 ዓ.ም ያ ቤት የሩጋ ትምህርት ቤት ተብሎ ተከፈተ፡፡

ከዚያ ትምህርት ቤት ገብቼ ነው እስከ ስምንተኛ ክፍል የጨረስኩት፡፡ በጣም ታታሪ ተማሪ ነበርኩ ሳቅ… ከክፍል አንደኛ እየወጣሁ ፡፡ በኋላ ደሴ ከተማ ወ/ሮ ስህን የገባሁት እዛም ከክፍል አንደኛ እየወጣሁ እስከ አስረኛ ክፍል ደረስኩ አስረኛ ክፍል ላይ ከ1-10 የወጡ ልጆች መምህራን ማሰልጠኛ እንዲገቡ ይደረግ ነበር፡፡

እኔም ከሌሎቹ አምስት ልጆች ጋር ሆነን አስመራ መምህራን ማስልጠኛ ገብቼ በ1961 እና በ1962 ዓ.ም አስመራ ተምሬ መምህራን ማስልጠኛ በዲፕሎማ ጨረስኩ እጣ ሳወጣ ሸዋ ጠቅላይ ግዛት ደረሰኝ መናገሻ አውራጃ ሜታ የሚባል ሜታቦ ቢራ ፋብሪካ ያለበት ጃራ የሚባል ትምህርት ቤት እንደደረሰኝ ሁለት ዓመት በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህርነት አገለገልኩ ሦስተኛውን ዓመት በስራ መሪነት አገለገልኩ፡፡

**ናይል፡-** ለሀገሪቱ እድገት የበኩሌን አስተዋፆ አድርጊያለሁ ካሉ ቢገልፁልን?

አቶ አሊ፡- ሰራሁ ብዬ የማስበው ሁለት ቦታ ነው፡፡ አንደኛው እድገት በህብረት የውቀትና የስራ ዘመቻ ነው፡፡ ይህ ዘመቻ ትልቅ ስራ የተሰራበት ነው፣ ወደ ገበሬው በመግባት ወጣቱ የህይወት መስዋዕትነት በማድረግ ገበሬውን ለመጀመሪያ ጊዜ አደራጅቶ የገበሬውን ችግሮች ያየበት ነው፡፡

ወደ ገፅ 5 ዞሯል

# እንግዳ

ይህ አምድ የዩኒቨርስቲው ሰራተኞች፣ ተማሪዎች ወይም ሌሎች ታዋቂ እና ተፅኖ ፈጣሪ ሰዎች በዕንግድነት ይቀርቡበታል

**የዛሬው እንግዳችን የአሁኑ ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ የመምህራን ትምህርት አካዳሚ በነበረበት ወቅት ከ47 ዓመታት በፊት ከመጀመሪያዎቹ የዲግሪ ተማራቂዎች አንዱ የሆኑት አቶ አሊ ይመር ከበደ ናቸው፡፡ ስለቱባ የህይዎት ልምዳቸውና ስለቀድሞው የባሕርዳር ትምህርት አካዳሚ ትውስታቸው ያጫወቱንን እናካፋላችሁ፡፡ መልካም ንባብ**

**ናይል፡-** ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ በመሆንዎ በናይል ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ስም እያመሰግን ስምዎትንና የስራ ሃላፊነትዎን ቢያስተዋውቁን?

**አቶ አሊ፡-** አመሰግናለሁ አሊ ይመር ከበደ እባላለሁ አሁን ሰባ (70) ዓመት ሞላኝ፡፡ ከ47 ዓመት በኋላ ከተማርኩበት ትምህርት ቤትና የመጀመሪያ ድግሪዬን ካገኝሁበት ተቋም በህይዎት ተገኝቼ ይህንን ቃለምልልስ እንዳደርግ አፈላልጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ::

**ናይል፡** የህይወት ውጣ ውረድ ምን ይመስላል ቢያጫውቱን?

**አቶ አሊ፡** አመሰግናለሁ እኔ የ35 ዓመት ባለትዳር ነኝ፡፡ሳቅ… እንግዲህ የወርቅ ኢዩበልዩ ለማክበር 15 ዓመት ይቀረናል፡፡ ሳቅ… ሦስት ልጆች አሉኝ ሁለቱ የተሳካላቸው ውጤት ያላቸው ተማሪዎች ነበሩ፡፡ ኢንጅነር፣ ዶ/ር እና ሀኪም ሆነዋል፡፡

**ናይል፡** የኮሌጅ ህይዎትዎ እንዴት እንደነበር ያጫውቱን?


**አቶ አሊ፡** መቶ ሆነን 1966 ዓ.ም ንብረታችን አስረክበን መስከረም 16/1966 ዓ.ም ገደማ የመምህራን ትምህርት አካዳሚ ለመቀላቀል ባሕር ዳር ገባን ፣በዛን ጊዜ ምንም አይነት ግንባታ አልነበረም አልፎ አልፎ የመምህራን መኖሪያ ተከለው ላይብራሪው ሪጅስትራርና ኦዲዬቪዥዋል ህንጻዎችና መሰብሰቢያ አዳራሹ እና ምግብ ቤቶች ገና ግንባታ ላይ ነበሩ:: መንገዱ ኮረኮንች ነበር፡፡ መኝታ ስለሌለ ፖሊ ቴክኒክ ነበር ያስቀመጡን መማሪያ ክፍሉም እዛው ነበር::

አንድ ዓመት ፖሊ ቆየን ሁለተኛ ዓመት ላይ ያን ጊዜ ህዝባዊ ኑሮ ርባታ የሚባል የብሔራዊ አገልግሎት ነበር፤ እሱን ለመወጣት አራት ወር መምህራን ማሰልጠኛ ረዳት መምህር ሆነን ለማሰልጠን ገብተን ሰርተን እነሱ የሚሰጡትን የግምገማ ውጤት ይዘን መምጣት ነበረብን፡፡በወቅቱ እኔ አራት ወር መምህራን ማሰልጠኛ ረዳት ሳይኮሎጂ ኢንስትራክተር ሆኜ ሰራሁኝ ጥር ላይ እድገት በህብረት የእውቀትና የስራ ዘመቻ ታወጀ፡፡

**ናይል፡** ያሁኑ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለምን ዓላማ ተቋቋመ? በወቅቱስ የመግቢያ መስፈርቱ ምን ነበር?

**አቶ አሊ፡** በወቅቱ 10ኛ ክፍል ላይ ከ1 እስከ 5 የሚወጡ ተማሪዎች መምህራን ማሰልጠኛ ይገቡ ነበር፡፡ ለመምህራን ትምህርት ልዩ ትኩረት ይሰጥ ነበር፡፡

የባሕር ዳር መምህራን ትምህርት አካዳሚ በሀይለስላሴ ጊዜ ነው የተቋቋመው አላማው የመምህራን የትምህርት ብቃትን ማሟላት ነበር:: የተቋሙ የምልመላ መስፈርት፤ አንደኛ ደረጃ ት/ት ቤት የስራ መሪ ሆኖ እየሰራ ያለ፣ በትንሹ የ3 ዓመት አገልግሎት ያለው ወይም ሱፐር ቫይዘር የሆነ ነው ብለው ማስታወቂያ አወጡ፡፡ በወቅቱ ተወዳዳሪው እጅግ በጣም ብዙ ነበር:: ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች መካከል መስፈርቱን ያሟላንና ማዕቀፍ ውስጥ የገባን አስር እጩ ተመዝጋቢዎች የጽሑፍ ፈተና ቀረብን፡፡ እኔ አዲስ አበባ ወሰን ሰገድ ት/ቤት ነበር የተፈተንኩት፡፡ በወቅቱ ባሕር ዳር መጥተን ፈታኞች ሚስተር ሚንዳ የተባለ የእንግሊዘኛ መምህር የሖነ አሜሪካዊና አቶ ሀይሉ ጽጌ የስዕል ባለሙያ፣ ምን አልባት ታውቋቸው ከሆነ ሁለቱ ነበሩ ሊፈትኑን የመጡት፡፡ በዛን ጊዜ የነበረን መስፈርት ከአሁኑ ጋር እንድታወዳድሩት ብየ ነው የማነሳላችሁ፡፡ አንድ የጽሑፍ ፈተና ይቀርባል በዛ ላይ እያንዳንዳችን ያለንን አስተያየት እንሰጣለን፡፡ አንድ ት/ቤት ለማስተማር ተቀጥረህ ታስተምራለህ ት/ት ቤቱ አጥር የለውም አውሬውም ምኑም ይገባል ያን ት/ት ቤት ማሳደግና የልጆቹን ደህንነት እንዲጠበቅ ይፈለጋል እንደ ስራ መሪ፣ እንደ ስታፍ ምን ታደርጋለህ? የሚል ጥያቄ ነበር የቀረበልኝ እዛ ላይ አስራችን ተፋጠን አንድ ሰው ነበር የሚያስፈልገው ማን ምን ማድረግ እንዳለበት ሁሉም የራሱን ሀሳብ አቀረበ:: ካስሩ መካከል እንግዲህ በሰጠሁት መልስ



አቶ አሊ ይመር ከበደ ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ የመምህራን ትምህርት አካዳሚ በነበረበት ወቅት የመጀመሪያ ተመራቂ

ይሁን አላውቅም ሳቅ… አንደኛው ተመራጭ እኔ ሆንኩ፡፡ ያንጊዜ በየጠቅላይ ግዛቱ መምህራን በዚህ ዓይነት ተፈትነው ነበር የገቡት፡፡

**ናይል፡** ድሮ መምህራን ት/ት ኮሌጅ በገቡበት ጊዜና አሁን ያለውን የባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ ሁኔታ በንጽጽር ቢገልጹልኝ?

**አቶ አሊ፡** በጣም ጥሩ እኔ ያን ጊዜ የሚጠራው ባሕር ዳር መምህራን ኮሌጅ አይደለም የባሕር ዳር ትምህርት አካዳሚ ነበር የሚባለው፡ ፡ እንግዲህ ያን ጊዜ ስንገባ አመራረጡን አጫውቸሃለሁ በዛ ሁኔታ የተመረጡ ሙያውን ለሚወዱ እውቀቱም ያላቸው ግማሽ ሰራተኛ ቦታ ነበር ችግሩንም ያሳለፉ ቤተሰብንም መስርተው ያዩ ሰዎች ናቸው የገቡት፡፡

መምህራን ማሰልጠኛዎችን ለማጠናከር ታስቦ ነው የገቡት ሰልጣኞች ሲጨርሱ የሚመለሱት የመምህራን ማሰልጠኛዎች ነው:: የመምህራን ማሰልጠኛ የአንደኛ ደረጃ መምህራን በጥራት መውጣት አለባቸው ተብሎ የተከፈተ አካዳሚ ነበር፡፡ መምህራን ትምህርት አካዳሚ ጨርሰን ስንወጣ ወደ መምህራን ማሰልጠኛ ነው የሄድነው እና እሳቤው የትምህርት ጥራት ለማስጠበቅ መምህራንን ማብቃት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ በዚህም ቆይታችን ያንን ብቃት እንድናገኝ አድርጎናል:: የሰጡን ትምህርት ተግባር ተኮር ነበር፡፡ በዚያን ወቅት ፋሲሎ ከነገደ ወይጦዎች ሂደን የሚሰፉትን ስፌት የሚሰሩትን ሸክላ ጥናት እያጠናን እንመጣ ነበር፡፡ ወረቀት የሚሰራው ከዛ ላይ ነበር፡፡ ማህበረሰቡ ጋር ሂደን ህብረተሰቡ ምን ይሰራል? ህብረተሰቡ የጎደለው ምንድን ነው:: እኛ ሰልጥነን ምን አስተዋጽኦ ማድረግ እንችላለን የሚሉ ነገሮች ላይ እናተኩር ነበር፡፡ህብረተሰቡ ጋር ሁነን ተምረናል ማለት እችላለሁ ክፍል ውስጥ ሁነን አልጨረስንም::

በዚያን ወቅት የእኛ ጓደኛ የሆነ አንሙት በቀበሌ 7 አካባቢ ያሉትን ገበሬዎች ሰብስቦ የተለያዩ የከብት እርባታ በተመለከተ ገበሬዎች በማደረጃት የሰራቸው ስራዎች ኮሌጁ እራሱን ችሎ ከብት እንዲያረባ ምክንያት ሆኖታል፡፡ በወቅቱ የነበርነው ተማሪዎች ሁል ጊዜ ፕረዘንት እናደርጋለን፡፡ ከመካከላችን ማነው ጎበዝ ሱፐርቫይዘር የሚል ርዕስ ይሰጣል አንዱ ሦስት ሳምንት ከሆነ ርዕሱ ለኔ ሊደርሰኝ ይችላል፡፡ ጥሩ ሱፐርቫይዘር ማነው ብዬ ፈልጌ አፈላልጌ አንብቤ ወረቀት አቀርባለሁ በዚህ መልኩ በሚሰጠው ትምህርት አካዳሚው የተሳካለት እንደነበር አስታወሳለሁ፡፡ በዛ ተቀርጨ ስለወጣሁ በህይወቴ ብዙ ስራዎችን እንድሰራ ረድቶኛል፡፡

ሌላው ትንሽ መኝታ ቤቶች፣ ካፍቴሪያው፣ከላይ የአስተዳደር

ወደ ገፅ 14 ዞሯል










*Bahir Dar University Sport Accademy Photo Essay*